የፍትሀብሄር ስነ-ስርዓት ህግ ስልጠና

ግንቦት

2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

መግቢያ

የፍትሀብሄር ፍትህ አስተዳደር ዋና ዋና ግቦች

በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡ ውሳኔዎች

- ውጤታማ
- ታዓማኒ
- ፍትሀዊ
- ተገማች
- ሚዛናዊ
- ተደራሽ
- ቀልጣፋ እንዲሆኑ ማድረግ ማስቻል

የቀጠለ

- ✓ከላይ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲኖሩ
- ኢንቨስትመንት ያድጋል
- ዜጎች ተጨማሪ ሀብት ይፈጥራሉ
- አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ይፈጠራሉ፣ ይሻሻሉ፣ ወደሀገር ውስጥ ይገባሉ
- የስራ እድል ይፈጠራል
- ዜጎች ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ እውቀታቸውን ስራ ላይ ማዋል ይችላሉ

የቀጠለ

እነዚህን ግቦች ለማሳካት

- በቂ፣ የሰለጠነና ሙያዊ ስነ ምግባር ያለው የሰው ሀይል ማሞላት
- ፍርድ ቤቶችን በመሰረተ ልማት ማሞላት
- ፍርድ ቤቶችን ተደራሽ ማድረግ
- ፍርድ ቤቶችን ከማንኛውም ተጽእኖ ነጻ እንዲሆኑ ማድረግ ወዘተ ያስፈልጋል(ውጫዊ፣ወይም ውስጣዊ)

የፍትሀብሄር ስነ-ስርዓት ህጉና ህገ መንግስቱ

- ✓በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37(1) ስር

ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊያልቅ የሚችልን ጉዳይ ወደ ፍርድ ቤት በመሰውድ ፍትህ የማግኘት መብት እንዳለው ተመልክቶል። አንድ ሰው በህግ ፣ በውል ወይም በፍርድ ደተረጋገጠ መብት ያለው ሲሆን ነው።

- ✓በዚሁ ህግ ንኡስ ቁጥር 2(ሀ፣ ለ) ስር ያለውን ይመልከቱ

የቀጠለ

- ✓ በፍርድ ቤት የቀረበ ጉዳይ የክስ ምክንያት አለው ብሎ ለመወሰን የሚቻለው በክሱ ላይ የተገለጸው ነገር ቢረጋገጥ ከሳሹ የጠየቀውን ለማግኘት ህግ የሚፈቅድለት የሆነ እንደሆነ ሲሆን ነው።
- ✓ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ እና ውሳኔ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 37) መዝ.ቁ. 136775 (ቅጽ 21)

የቀጠለ

- ✓ አንድ ጉዳይ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው ክስ ከሆነና ጉዳዩን ለማየት በህግ በግልጽ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው ሌላ እስከሌለ ድረስ በፍርድ ቤት ቀርቦ ሊስተናገድና ውሳኔ ሊሰጥበት የሚቻልበትና የሚገባ ስለመሆኑ አንቀጽ 37(1) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 79(1) መዝ.ቁ. 80202 (ቅጽ 15)

የቀጠለ

- የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40 ላይ ዜጎች የንብረት መብታቸው የተጠበቀ እንደሆነ ያመለክታል። ይህ መብት የህዝብን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል በሌላ ህግ ካልተወሰነ በስተቀር ንብረት የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የማስተላለፍ፣ የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍን ይጨምራል ሲል ያስቀምጣል።

የቀጠለ

- በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 43 ስር ሁሉም ዜጎች በጋራም ሆነ በተናጥል የመልማት እና የማያቆርጥ የእድገት ሂደት ውስጥ የማለፍ መብት ያላቸው መሆኑ ተደንግጎል።
- ✓ ሰዎች በማህበራዊ ሁኔታዎች ውስጥ ሲኖሩ ያላቸውን ይሰጣሉ የሌላቸውን ይቀበላሉ። ብዙ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ሁሉ ከሌሎች ያገኛሉ። ታዲያ ይህ ሂደት አስተማማኝ እንዲሆን፣ በንብረቶቻቸው ላይ ያላቸው መብቶች ዋስትና እንዲኖረው የልውውጥ ስርዓቱን የሚገዛ የፍትህ ስርዓት ያስፈልጋል።
- ✓ የፍትህብሄር ፍትህ ስርዓት መኖር ግብይቶችን አስተማማኝ፣ ዋስትና ያላቸው እንዲሆኑ ያደርጋል።

የቀጠለ

- ✓ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 78 ስር የዳኝነት አካል ስለመመስረቱ
- ✓ በዚሁ ህገመንግስት አንቀጽ 79 ስር ፍርርድ ቤቶች የዳኝነት ስራ ሲሰሩ ከየትኛውም አካል ነጻ ስለመሆናቸው

የፍትሀበሄር ስነ-ስርዓት ህግ ምንነት

- የስነ-ስርዓት ህግ ሰዎች በፍርድ ቤት ወይም በህግ የመዳኘት ስልጣን ለተሰጣቸው አካላት የሚቀርቡ አቤቱታዎች /ክሶች/ የሚመሩበትን ስርዓት የሚደነግግ ነው
- ባጠቃላይ ሙግት የሚመራበትን ስርዓት የሚዘረጋ ነው። (ተከራካሪዎችም ፣ፍርድ ቤትም ክርክርን የሚመሩት) በስነ-ስርዓት ህጉ መሰረት ነው።

የቀጠለ

- ✓ አቤቱታ መቼ፣ እንዴት፣ በማን ይቀርባሉ የሚሉትን ጉዳዮች ያስቀምጣል
- ✓ የፍትሀብሄር ስነ-ስርዓት ህግ ዜጎች በመደበኛ ህግ/substantive laws/ ያገኟቸውን መብቶች የሚያረጋግጡበት ስርዓት በመሆኑ መዳረሻ /means/እንጂ በራሱ ፍትህ /justice/አይደለም የሚሉ ወገኖች አሉ።
- ✓ በጠቅላላው የአቤቱታና መልስ አቀራረብን፣ የማስረጃ አቀራረብ ስርዓት፣ የክርክር አመራር ስርዓትን፣ የፍርድ አፈጻጸምንና የይግባኝ /የሰበር/አቀራረብን የሚመለከቱ ስርአቶችን የያዘ
- ✓ Is the civil procedure a means to implement the rights on the substantive law or it is an end? Some say there is procedural justice

የቀጠለ

የመወያያ ጥያቄዎች

1. በህገ መንግስቱ አንቀጽ 37(2(ሀ፣ለ)) ስር ያለውን ከፍትሀብሄር ስነ-ስርዓት ህጉ አንቀጽ 67፣34፣38፣ከ 57-63 (በፍርድ ቤት ክርክር የሚያደርግ ሰው ጥቅም ያለው/ ባለመብት/ ወይም ውክልና ያለው ሰው መሆን ያለበት ስለመሆኑ) ከሚያስቀምጠው ጋር አንቀጽ 37(2) እንዴት ይሄዳል ማለትም

የቀጠለ

- በሞተ ሰው ስም ቀደም ብሎ የተሰጠን ውክልና በመያዝ የሚቀርብ ክስ፣ የሚደረግ ክርክር እና የሚሰጥ ውሳኔ እንዳልተወሰነ የሚቆጠር ስለመሆኑ የፍ/ህ/ቁ. 223291) የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 57

የቀጠለ

አንድ ማህበር የአባላቱን የጋራም ሆነ የግል ጥቅም ለማስጠበቅ አባላቱን በመወከል የዳኝነት ስልጣን በተሰጣቸው አካላት ዘንድ ቀርቦ ለመከራከር እንደሚችል የህገመንግስቱ አንቀጽ 37(2) ይደነግጋል። እርስዎ ባሉበት ችሎት አንድ ማህበር የአባሉን ጥቅም ለማስጠበቅ አባሉን ወክሎ ለመከራከር ቢቀርብ ይፈቅዳሉን

የቀጠለ

2. ለምሳሌ አንድ መንግስታዊ ያልሆነ ሲቪክ ማህበር የሁሉንም ሰው ጥቅም የሚነካ ተግባር መፈጸሙን ጠቅሶ ከማንም ሰው የተሰጠ ውክልና ሳይኖረው ነገር ግን የራሱ መተዳደሪያ ደንብ ይህን ክስ እንዲመሰርት እንደሚፈቅድለት ገልጾ ክስ ቢመሰረት ተቀባይነት ይኖረዋል
3. ክርክርን በአግባቡ ለመምራት የፍትሀብሄር ስነ-ስርዓት ህግ ድንጋጌዎች መከበር ይኖርባቸዋል። የስነ-ስርዓት ህግን ድንጋጌዎች ለማክበር ሲባል የዜጎች መሰረታዊ መብቶች ቢጣሱስ ችግሩ እንዴት ይፈታል።

የዳኝነት ስልጣን

- የዳኝነት ስልጣን የመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም በህግ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ሊኖራቸው ይችላል።(የ.ፍ.ስ.ስ.ህ.ቁ. 4)
- ✓ሌሎች አካላት ለምሳሌ፦ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ
- ✓የደሬደራልና የክልል የግብር ጉዳዮችይግባኝ ኮሚሽን
- ✓የከተማና የገጠር መሬት የካሳ አወሳሰን ቅሬታ ሰሚ ኮምቴ/ይግባይ ሰሚ ኮምቴ/ የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ

የክስ አመሰራረት፣ አቤቱታን ስለማሻሻል እና ተከራካሪዎችን መጣመር

- ❖የክስ አመሰራረት
- ✓የፍትሀብሄር ክስ የሚጀምረው ከሳሽ ክሱን/አቤቱታውን/ ለመዳኘት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሲያቀርብ ነው (ስልጣን ብሄራዊ የዳኝነት ስልጣን፣የአከባቢ ስልጣን፣ የስረ-ነገር ስልጣንን ይይዛል)(የፍ.ስ.ስ.ህ.ቁ. 9፣10፣አንቀጽ 229፣231፣244)

የቀጠለ

- ✓ ዳኝነት ባልተጠየቀበት ጉዳይ የሚሰጥ ፍርድ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ አንቀጽ 182(2) መዝ.ቁ. 33945(ቅጽ 8)
- ✓ አንድ ክስ ሲቀርብ በክስ ማመልከቻው ላይ መግለጽ ከሚገባቸው ነገሮች መካከል አንዱ የክሱ ምክንያትና ለክሱ ምክንያት የሆኑት ነገሮችና እነዚሁ የተፈጠሩበት ጊዜና ስፍራ ስለመሆኑ አንቀጽ 80(2)፣ 231(1)፣ 216(1)፣222(1-2) ያመለክታሉ። መዝ.ቁ. 91329(ቅጽ 16)

የቀጠለ

የግዛት ክልል ስልጣን

- ✓ የግዛት ክልል ስልጣን የሌለው ፍ/ቤት ጉዳዩን መመለስ ይኖርበታል (10(1) እና 231)
- ✓ የግዛት ክልል ስልጣን መቃወሚያን ውድቅ ባደረገ ፍ/ቤት ላይ ይግባኝ አይቀርብም(ሆኖም ውሳኔው ፍትህን የሚያዛባ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር)
- ✓ አንድን የፍትሀብሄር ክስ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በበለጡ ፍርድ ቤቶች ዘንድ ለማቅረብ የሚቻል ሲሆን የክሱ ማመልከቻ በቀደምትነት የቀረበበት ፍርድ ቤት ብቻ የዳኝነት ስልጣን እንዳለው ተቆጥሮ ለክርክሩ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ

የቀጠለ

- ✓ ፍርድ ቤቱ የግዘት ክልል ስልጣን የለውም በማለት ለሚቀርብለት መቃወሚያ የሚሰጠው ውሳኔ ፍትህን የሚያጓድል ካልሆነ በቀር ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል ስለመሆኑ አንቀጽ 10(2) መዝ.ቁ. 109383(ቅጽ 19)

በግዛት ክልል ክስ የሚቀረብበት ሁኔታ

- ✓ አንቀጽ 19 ተከሳሹ በሚኖርበት ወይም ለግል ጥቅሙ በሚሰራበት ክፍል ባለው ፍ/ቤት
- ✓ አንቀጽ 20 ተከሳሹ የሚኖረው ወይም ለግል ጥቅሙ የሚሰራው ከኢትጵያ ግዛት ውጭ በሆነ ጊዜ ከሳሹ በመረጠው በአንዱ ፍርድ ቤት ይሆናል። ለክሱ መነሻ የሆነው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሲሆን ንብረቱ በሚገኝበት ፍ/ቤት
- ✓ የግዛት ክልል ስልጣን ከአንቀጽ 19-30 ባሉት ድንጋጌዎች መሰረት ይመራል።

የቀጠለ

- ✓ አንቀጽ 25 የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሚመለከት

ክርክሩ የተነሳው አዲስ አበባና አማራ ክልል በሚኖሩ ሰዎች መካከል ቢሆንና ንብረቱ የሚገኘው አማራ ክልል ቢሆን ክስ ሊቀርብ የሚገባው የትኛው ፍ/ቤት ነው

ጉዳዩን ለማየት የውክልና ስልጣን በተሰጠው የክልል ፍ/ቤት ሊቀርብ ይገባል በሚል ተወስኖል።

- ✓ በየክልሎቹ የከተማ ነክ ፍ/ቤቶች ማቆቆሚያ አዋጆች ላይ የከተማ ቦታን በሚመለከት በተሰጣቸው ስልጣን ተፈጻሚ የሚሆነው የከተማ ነክ ፍ/ቤቶችን ለማቆቆም የወጡት አዋጆች ናቸው (በአንቀጽ 25 መሰረት) ለምሳሌ ካርታ ይሰረዝ፣ ካርታ ይሰራልኝ ወዘተ

የቀጠለ

- ✓ለአንድ ክርክር መነሻ የሆነ ቤትና ይዞታ በክልል የሚገኝ ሲሆንና ስረ ነገር ስልጣኑ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቢሆንም ጉዳዩ መታየት ያለበት ንብረቱ በሚገኝበት ክልል/ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ መዝ.ቁ 139942 (ቅጽ 22)

የቀጠለ

- ✓አንቀጽ 21 በመንግስት ላይ የሚቀርብ ክስ

ሀ. ከሳሽ በሚኖርበት ወይም ለግል ጥቅሙ በሚሰራበት

ለ. ለክርክሩ መነሻ የሆነው ውል በተፈረመበት፣ ውሉ ሊፈጸም በታቀደበት

ሐ. ሐላንትን ያስከተለው ወይም ለክሱ መነሻ የሆነው በተፈጸመበት ክፍል ባለው ፍ/ቤት

የቀጠለ

- ✓ አንቀጽ 22 በንግድ ድርጅቶች ላይ ፣ በማህበር ወይም ኮሚቴ ወይም በአደራ ንብረት ጥበቃ የሚቀርብ ክስ የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት ወይም ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ባለው ፍ/ቤት ወይም ማህበሩ ወይም ኮሚቴው ወይም ድርጅቱ በተመሰረተበት ወይም እንዲመዘገብ በተወሰነበት አካባቢ ባለው ፍ/ቤት

የቀጠለ

- ✓ አንቀጽ 23 በውርስ ምክንያት የሚቀርብ ክስ ውርሱ በተከፈተበት አካባቢ ባለው ፍ/ቤት
- ✓ አንቀጽ 24 በውል ምክንያት የሚቀርብ ክስ በከሳሽ ምርጫ ውል በተዋዋሉበት፣ ውሉ እንዲፈጸም በተስማሙበት ባለው ፍ/ቤት
- ✓ 24(3) ኢንሹራንስን የሚመለከት ከሆነ የኢንሹራንስ ድርጅቱ ባለው ዋና መስሪያ ቤት ወይም ድርጅቱ በኢትዮጵያ ግዛት በተመዘገበበት፣ በሚሰራበት፣ ውሉ የተደረገበት ሀብት በሚገኝበት ባለው ፍ/ቤት

የቀጠለ

- ✓ አንቀጽ 24(4) በመያዣ፣ በተቀማጭ ወይም በአደራ በተሰጠ ንብረት ምክንያት ሲሆን ንብረቱ በሚገኝበት አካባቢ ባለው ፍ/ቤት
- ✓ አንቀጽ 27 ከውል ውጭ በደረሰ ጉዳት ከሆነ ጉዳቱ በደረሰበት ስፍራ ይቀርባል
- ✓ አንቀጽ 28 በመኪና ክስ ላይ የከሰረው ሰው ወይም ድርጅት በሚገኝበት ቦታ

የቀጠለ

- የስረ-ነገር ስልጣን
- ✓ የፍርድ ቤቶችን የስረ ነገር ስልጣን ለመወሰን በዋናነት የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234 ፣የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80፣ የየክልል ፍርድ ቤቶች ማቆቆሚያ አዋጆች፣ የከተማ ነክ ፍ/ቤቶች ማቆቆሚያ አዋጆች፣ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ፣ የቤተሰብ ህግ ሌሎች አዋጆችን መሰረት በማድረግ የሚወሰን ነው።

የቀጠለ

- ✓ የስረ ነገር ስልጣን የክስ መቃወሚያ ሲሆን ተከራካሪዎች ባያነሱትም ፍ/ቤት ሊያነሳው የሚገባ ነው። (አንቀጽ 231፣244)
- ✓ አንድ የዳኝነት አካል የሥረ- ነገር ስልጣን ባይኖረውም

እንኳን የሰጠው ውሳኔ ሥርዓቱን ተከትሎ እስካልተሻረ ድረስ የፀናና የመጨረሻ በመሆኑ አዲስ ክስ በተመሳሳይ ጉዳይ ማቅረብ ተገቢ ስላለመሆኑ፣ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5/1/ እና 212 መዝ.ቁ 105677(ቅጽ 20)

የቀጠለ

- ✓ አንድን ጉዳይ ለማየት በህግ ስልጣን የሌለው ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ በይግባኝ ታይቶ እንዲታረም ካልተደረገ በቀር በጉዳዩ ላይ አስገዳጅነት ያለው ስለመሆኑ አንቀጽ 212 መዝ.ቁ. 85718(ቅጽ 15)
- ✓ በመርህ ደረጃ በህግ የተቋቋመ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በህግ አግባብ በተቋቋመ የበላይ ፍርድ ቤት በህጉ በተዘረጋው ስርዓት እስካልተለወጠ ድረስ የማይፈጸምበት ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ አንቀጽ 378፣ 372፣ 392፣መዝ.ቁ. 101345(ቅጽ 17)

ክርክሮችንና ተከራካሪዎችን ስለማጣመር

- ✓ አንቀጽ 11 እና 17 ተከራካሪዎቹ አንድ ሲሆኑ
- ✓ ተመሳሳይ የህግና የፍሬ ነገር (የስረ ነገር ጭብጥ) ሲኖር
- ✓ የፍ.ስ.ስ.ህ.ቁ. 35፣36፣37 ተከሳሾች ወይም ከሳሾች የሚጣመሩበትን ሁኔታና ክርክርን በጋራ ስለማቅረብ ያስቀምጣል
- ✓ ከአንድ በላይ ከሳሾች ወይም ከአንድ በላይ ተከሳሾች በአንድ ክርክር ተሳታፊ በሚሆኑ ጊዜ ክርክሩ ስለሚመራበት ሁኔታ

የቀጠለ

- መዝ.ቁ. 139313
- አንድ ከሳሽ መብቱን ማግኘት የሚገባው ከየትኛው ተከሳሽ ላይ እንደሆነ ለይቶ ለማወቅ የሚያጠራጥር ሁኔታ ያጋጠመው ሲሆን አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎችን በህብረት በመክሰስ ሀላፊነቱ የሚመለከተው ከየትናው እነደሆነ ተለይቶ አንዲወሰንለት ማመልከት ስለመቻሉ
- ፍርድ ቤቶች በአንድ ክስ ላለለ ስማቸው ከተጠቀሱት ውስጥ የትኛው/የትኞቹ ሀላፊ እንደሆኑ እንዲወሰንለት ማመልከት ስለመቻሉ

የቀጠለ

- ✓ ፍርድ ቤቶች በአንድ ክስ ስማቸው በተከሳሽነት ከቀረቡ መካከል ስማቸው ከመጠቀሱ ውጭ በግልጽ ዳኝነት አልቀረባበቸውም በሚል ብቻ አንዱን ወይም የተወሰኑትን ሀላፊነት የለባቸውም በማለት የሚደርሱበት መደምደሚያ ህጉን የተከተለ ስላለመሆኑ የፍ/ስ/ስሀ.-ቁ. 36(5)

የቀጠለ

- በአንድ ክርክር ውስጥ የከሳሾች ወይም የተከሳሾች ብዛት ከአንድ በላይ ሲሆንና ክርክሩም ከሳሾችን ወይም ተከሳሾችን በአንድ ዓይነት መልክ የሚመለከታቸው ሲሆን ከሳሾቹ ወይም ከተከሳሾቹ አንዱ በጠቅላላው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ሲጠየቅና ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤት ፍርዱን በመለወጥ ያሻሻለው ወይም የለወጠው ወይም ያጸናው ፍርድ ይግባኙን ባላቀረቡት ከሳሾች ወይም ተከሳሾች ላይም በይግባኝ ደረጃም በቀረበው ጉዳዩ ከከሳሾቹ መካከል አንዱ ይግባኝ ጠይቆ የሚሰጠው ውሳኔ ሌሎችንም የሚያካትት ስለመሆኑ አንቀጽ 35 እና 331 መዝ.ቁ 139138(ቅጽ 22)

የቀጠለ

- ✓ አንድን ጉዳይ በተመለከተ ተከራካሪ ወገኖች በየበኩላቸው በተለያዩ ፍርድ ቤቶች (ችሎቶች) አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ ክሶች ባቀረቡ ጊዜ (የክርክሮቹ ደረጃ) ምንም ይሁን ምን) ከሳሾቹ ተጣምረው ሊወስኑ የሚገባ ስለመሆኑ 8(1)፣ 11፣ 244፣ 245 መዝ.ቁ. 81275 (ቅጽ 15)

ክርክርን በወኪል፣ በነገረፈጅ ስለመምራት

- አንቀጽ 34(ውክልና፣ እንደራሴ፣ ሞግዚት)
- አንቀጽ 38 በነገረፈጅ፣ አንቀጽ 57-68 በውክልና የሚደረግ ክርክር
- አንቀጽ 38 ላይ የተጠቀሰው ስለሌሎች መወከል ከህገመንግስቱ አንቀጽ 37 ጋር አንዴት ይታያል።
- አንድን ሰው በመወከል በፍርድ ቤት ቀርቦ ለመሟገት በህጉ የተቀመጠውን ዝምድና ደረጃ ወይም የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ ውክልና የሚያስፈልግ ስለመሆኑ 7(2)፣ 32፣ 57፣ 58፣ 63 መዝ.ቁ. 131622

የቀጠለ

- አንድ ሰው በፍርድ ቤት የሚከራከረው በራሱ፣ በጠበቃ፣ በወኪል፣ በነገረፈጅ፣ በሞግዚት ሊሆን እደሚችል ከስነ-ስርዓት ህጉ አንቀጽ 57 ያስቀምጣል። ነገር ግን እነዚህ የሚመነጩት ከውክልና ህግ ስለሆነ በወካይ እና በተወካይ መካከል ባለው የሚኖረው ግንኙነት በውክልና ህጉ የሚመዘን ነው። በተለይም የጥቅም ግጭት እዳይፈጠር ጥንቃቄ ሊደረግ የሚገባው ነው።

የቀጠለ

- ✓ በሞተ ሰው ስም ባለ ውክልና በፍርድ ቤት ተተደረገ ክርክር፣ የተሰጠ ውሳኔ፣ብይን ወይም ትእዛዝ አንዳልተሰጠ የሚቆጠር ነው።

የክስ አመሰራረት

- ✓ ከሳሽ ክሱን በፍ.ስ.ስ.ህ.ቁ.222 መሰረት
- ✓ ክሱ የሚቀርብበትን ፍርድ ቤት ስምና የሚያስችልበትን አድራሻ፣ የክሱን አርእስት፣ የተከራካሪዎችን ስምና አድራሻ፣ ከሳሽ ወይም ተከሳሽ በህግ ችሎታ ያለው ስለመሆኑ፣ ከሳሽ ክሱን በጠበቃ ወይም በወኪል ከሆነ ክሱን ለማቅረብ ያለውን ስልጣን፣ ተከሳሹ ለክሱ ሀላፊ የሚሆንበትን ምክንያት፣ ለክሱ ምክንያት የሆነው ነገር በገንዘብ የሚገመት በሆነ ጊዜ ግምቱን፣ ከሳሽ የሚጠይቀውን ዳኝነት ያካተተ መሆን ይኖርበታል። (አንቀጽ 80፣222፣224)

የቀጠለ

- ✓ የክስ አቀራረብ ስርዓቱን ተከትሎ ያልቀረበ ክስ ፍርድ ቤቶች ሌላኛውን ወገን ሳይጠሩ ለመዝጋት ስለመቻላቸው አንቀጽ 33፣80፣222፣225፣226፣231 (መዝ.ቁ. 839159ቅጽ 15)
- ✓ አንድ ፍርድ ቤት ክስ ቀርቦለት ጉዳዩን ለማየት የሰረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን የዘጋው እንደሆነ ዋናውን ክርክር እንዳላየ የሚያስቆጥር ሲሆን በመዝገቡ ላይ የሰጣቸው ማናቸውም ትእዛዞች በማናቸውም ወገን ላይ ህጋዊ የሆነ ውጤት የሌለውና በዚሁ ጉዳይ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሲቀርብ ከዚህ ቀደም በፍርድ አልቋል ተብሎ ሊቀርብ የሚገባ ስላለመሆኑ (የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 5፣9፣231) መዝ.ቁ 100295(ቅጽ 21)

የቀጠለ

- ✓ ከሳሽ የሆነ ወገን የሚያቀርበውን የዳኝነት ጥያቄ አይነትና መጠኑን በክሱ ማመልከቻ በግልጽ በማስፈር ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ
- ✓ ተከራካሪ ወገኖች በህግ የተፈቀደ መፍትሄውን ለማግኘት በግልጽ ዳኝነት መጠየቅ የሚገባቸው ስለመሆኑ
- ✓ ዳኝነት የሚጠየቅብት መብትና ጥቅም በግልጽ ተለይቶ ያልተመለከተበት አቤቱታ የክስ ምክንያት እንደሌለው የሚቆጠር በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ አንቀጽ 33፣231 (መዝ.ቁ. 38419 ቅጽ 8)

የቀጠለ

- ✓ በክስ አቀራረብ ስርዓት ላይ ጉድለት ያለበት መሆኑ ተረጋግጦ የተዘጋ መዝገብ ምንም ዓይነት ክስ እንዳልቀረበ የሚያስቆጥርና የይርጋ ጊዜ የሚቋረጥ ውጤት የሌለው ስለመሆኑ (የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 278(2-ሀ) እና (3) (መዝ.ቁ 123123(ቅጽ 21)

የቀጠለ

- ✓ ከሳሽ የሚጠይቀው ዳኝነት ከአንድ በላይ በሆነ ጊዜ ይህንኑ ሁኔታ በአግባቡ በክሱ ላይ ማስፈር ይኖርበታል።
- ✓ በተጨማሪም ከሳሽ ለክርክሩ ያስረዱልኛል የሚላቸውን ማስረጃዎች ሁሉ መዘርዝርና ለፍርድ ቤቱ ማቅረብ ይገባዋል። በከሳሽ መቅረብ የማይችሉ ማስረጃዎች ካሉ ይህንኑ ለፍ/ቤቱ በማሳወቅ ፍ/ቤቱ አንዲያስቀርብለት መግለጽ ይገባዋል። (አንቀጽ 145)

የሚቀርቡት ማስረጃዎችም

- ✓ አንድ ተከራካሪ ወገን በማስረጃነት የሚጠቅሳቸው ምስክሮች፣ ሰነዶች ወይም ሌላ አስረጂዎች በፍርድ ቤቱ በኩል በጭብጥነት ተይዞ ከሚፈታው ፍሬ ነገር ጋር አግባብነት ያለው እና በህግ ተቀባይነት ያለው እስከሆነ ድረስ ቀርቦ መሰማት ያለበት ስለመሆኑ አንቀጽ 111፣249 እና 257 (መዝ.ቁ. 38683(ቅጽ 8)

የቀጠለ

- ከሳሽ ያቀረበውን ክስ የፍ/ቤቱ መዝገብ ሹም(ሬጂስትራር) ተመልክቶ ህጉ በሚፈቅደው ፎርም የተዘጋጀና የአካባቢም ሆነ የስረ-ነገር ስልጣን የሌለው መሆኑን መርምሮ ጉድለት ከሌለበት ተገቢው የዳኝነት ተከፍሎ ፋይል እንዲከፈት ያደርጋል።(አንቀጽ 214-215) አቤቱታው ጉድለት ከተገኘበት ተስተካክሎ እንዲቀርብ ለከሳሹ ይመልሳል(አንቀጽ 229)

የቀጠለ

- ✓ አቤቱታው ህጉ በሚያስቀምጠው ፎርም መሰረት የተዘጋጀና በፍ.ስ.ስ.ህ.ቁ. 92-93 ባለው መሰረት በአቤቱታው በወኪሉ የተፈረመበት መሆኑ አቅራቢው ማረጋገጥ ይኖርበታል።
- ✓ የመወያያ ጥያቄዎች (ገጽ 20-21)

አቤቱታን ስለማሻሻል

- በፍ.ስ.ስህ.ቁ. 91. መሰረት አንድ ፍ/ቤት ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ማንኛውም ጊዜ ተከራካሪዎች ሲያመለክቱ ወይም በራሱ ጊዜ አቤቱታ እንዲሻሻል ሊያዝ ይችላል። ይህ ድንጋጌ በጠባቡ ሊተረጎም የሚገባው ነው። ለምሳሌ አዲስ ማስረጃ ለማቅረብ ማሻሻልን የሚጠቀሙ አሉ።
- በክስ ማሻሻል ስርዓቱና ዓላማ ቀድሞ ዳኝነት ከተጠየቀበት ጉዳይ ፈጽሞ የተለየ ጥያቄ ለማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ አንቀጽ 91፣342 (መዝ.ቁ 100475(ቅጽ 19)

የቀጠለ

- መዝ.ቁ. 15885 ቅጽ 1

  በመጀመሪያው ክስ ላይ መልስ የማቅርብ መብቱ የታለፈ ተከሳሽ ክሱ ይሻሻል ተብሎ ሲታዘዝ በተሻሻለው ክስ ላይ መልስ ልስጥ ወይም መልስ ይዘ ቢመጣ በመጀመሪያው ክርክር መልስ የማቅርብ መብትህ ታልፏል በማለት መከልከል ስነ-ስርዓታዊ አይደለም። አንቀጽ233 ተከሳሽ መጥሪያ ሲላክለት መልሱን ይዘ ካልቀረበ ክርክሩ በሌለበት የሚሰማ መሆኑን ፍርድ ቤቱ በሚልከው መጥሪያ ላይ እንደሚገልጽ ተመልክቷል።

የቀጠለ

- አንቀጽ 70(ሀ) ክርክሩ እንዲሰማ በተወሰነው ቀጠሮ ከሳሽ ቀርቦ ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ከቀረ ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩ እንደሚቀጥል ያስቀምጣል። ይህ በአማርኛው ቅጂ ላይ የተቀመጠው ሁለቱም ድንጋጌዎች ተመሳሳይ ትርጉም ያለቸው ይመስላል። በእንግሊዘኛው ቅጂ ላይ በአንቀጽ 70(ሀ) ስር ex-parte የሚልሲሆን በ233 ስር ያለው እንግሊዘኛ ቃል ደግሞ defalut proceeding የሚናገር ነው።

የቀጠለ

- የ233 ድንጋጌ ተከሳሽ መልሱን ባያቀርብም የጉዳዩ መሰማት እንደሚቀጥል (defalut proceeding) ከሚያሳይ በስተቀር ተከሳሽ ከክርክሩ እንደሚወጣ አያመለክትም። በ 70(ሀ) ስር በተገለጸው መሰረት ተከሳሽ ባይቀርብም እሱ በሌለበት (defalut proceeding) መቀጠል ሳይሆን ከክርክሩ መውጣትን (ex-parte) እንደሚደረግ በግልጽ ያስቀምጣል።

የቀጠለ

- መዝ.ቁ. 161736

  ለአንድ ክስ መሻሻል ወይም ለክርክሩ መለወጥ ቀደም ሲል የቀረብን የክስ ምክንያት በመቀየር ለመሞገት ማቅረብ ነገሩን ይበልጥ የሚያብራራ ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ነው በሚል ክስ እንዲሻሻል የሚፈቅድበት የህግ ምክንያት ስላለመኖሩ የፍ/ስ/ስ/ቁ. 91(1፣2)

የቀጠለ

- ✓ በመጀመሪያ በቀረበ የክስ መከላከያ መልስ ያልተካተትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መልስ አንዲሻሻል በሚል ፍ/ቤት በሰጠው ትእዛዝ መነሻነት ተካቶ ሲቀርብ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አንቀጽ 91፣244፣ መዝ.ቁ. 55973(ቅጽ 12)

የቀጠለ

- ✓ከሳሽ ያቀረበው ክስ እና የክሱ ዝርዝር ይዘት የተለያየ ሆኖ የተገኘ ከሆነ ፤ ጉዲዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ በማዘዝ ፤የክርክሩን ሂደት መምራት ያለበት ሰለመሆኑ፤ ፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 91(1) (መዝ.ቁ 122249 (ቅጽ 20)

ሶስተኛ ወገን ተከሳሽና ጣልቃ ገብነት

- ✓ ተከራካሪ ወገኖች ወደአንድ ክርክር የሚገቡበት አግባብ (አንቀጽ 39 ፣ 40፣41፣42፣43)ን መሰረት በማድረግ ነው።
- ✓ በፍርድ ቤት በመካሄድ ላይ ባለ በክርክር የግድ ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች በሚሰጠው ውሳኔ ጥቅማቸው/መብታቸው/ ሊነካ የሚችል የሆነ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ አንቀጽ 40 (መዝ.ቁ. 39540 (ቅጽ 8)
- ✓ **<u>ጣልቃ ገብ</u>**
- ✓ አንቀጽ 41 መብቴ ተነክቶል የሚል ባለመብት ወደክርክሩ ለመግባት የሚያቀርበው አቤቱታ የሚስተናገድበት ስርዓት ሲሆን ከ 358 ጋር አብሮ የሚታይ ነው።

የቀጠለ

- ✓ በአንድ ክርክር ከሳሽ የሆነው ወገን ጣልቃ በገባ ተከራካሪ ወገን ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር ከማንሳት የሚከለክልበት የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ አንቀጽ 39፣40፣41 (መዝ.ቁ. 135254)
- ✓ አንድ ሰው ቀድሞ በቀረበ ክርክር ጣልቃ ገብ በመሆን ክርክር ያቀረበ ወይም በጉዳዩ ተሳታፊ የነበረ መሆኑ በጣልቃ ገብነት በቀረበበት ክርክር ግልጽ ዳኝነት ባልተጠየቀባቸው ጉዳዮች በሌላ ጊዜ ክስ ለማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ በዚህ አግባብ የሚቀርብን ክስ በቀድሞው ክርክር ተጠቃሎ መቅረብ የነበረበትና ተከፋፍሎ ዳኝነት ሊቀርብበት አይገባም በሚል አቤቱታን ውድቅ በማድረግ የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ አንቀጽ 41፣216፣218 መዝ.ቁ 137401(ቅጽ 22)

የቀጠለ

- ✓ በክርክር ወቅት ጣልቃ ልግባ የሚለው ወገን በተከራካሪ ወገኖች መካከል ባለው ጉዳይ የሚሰጠው ውሳኔ የክርክሩ ተከፋይ ባይሆን በምን አግባብና መልኩ መብቱንና ጥቅሙን የሚጎዳ መሆኑና አዲስ ክስ በማቅረብ ለማስቀረት የማይችል መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ አንቀጽ 41(2) መዝ.ቁ. 95934 (ቅጽ 16)

የቀጠለ

- ✓ ሁለትና በላይ የሆኑ ሰዎች በሚከራከሩበት ጉዳይ በሚሰጠው ውሳኔ መብቴና ጥቅሜ ይነካል በሚል አቤቱታ አቅርቦ ወደክርክሩ መግባት የሚችል ሲሆን ይህ ሁኔታ መኖሩን መሳየት ይነርበታል። (አንቀጽ 41)

- ✓ በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነውን ወገን የሚጎዳ ውሳኔ የተላለፈው ጉዳዩን በተዋረድ ባየው የሰበር ችሎት በሚሆንበት ጊዜ ይህ በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነው ወገን አለኝ የመለውን መብት ለማስከበር ይችል ዘንድ መብቴን ተጋፍቷል በሚለው ሰው ላ በስሙ ቀጥታ ክስ በመመስረት መብቱን ከማስከበር ውጭ በአንቀጽ 358 መሰረት ተቃውሞውን ለሰበር የሚቀርብበት ሁኔታ ስላለመኖሩ መዝ.ቁ. 102056 (ቅጽ 19)

የቀጠለ

- ✓ አንድ ክርክር መጀመሩን ያወቀ ወገን የክርክሩን ውጤት ጠብቆ መብቱን የሚነካበት ሆኖ ባገኘው ጊዜ ከውሳኔው በኋላ የሚያቀርበው አቤቱታ በአንቀጽ 358 መሰረት ተቀባይነት የለሌው ስለመሆኑ አንቀጽ 358፣ 153(3)፣ 418-421(ቅጽ 12)

የቀጠለ

- ✓ጣልቃ በመግባት በክርክር ተሳታፊ ለመሆን ጠይቆ የተፈቀደለትና የጣልቃ ገብነት አቤቱታውን ለተከራካሪ ወገኖች ማድረስ ሲገባው ይህን ባለመፈጸሙ መብቱ ከተሰረዘበት በኋላ ፍ/ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ላይ በአንቀጽ 358 መሰረት የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ አንቀጽ 41፣358 መዝ.ቁ. 40229(ቅጽ 9)

የቀጠለ

- ✓ በአንድ ጉዳይ በከሳሽነት በተሰየሙ ወገኖች መካከል በተካሄደ ክርክር የተሰጠ ፍርድ ጋር በተያያዘ መብት ወይም ጥቅም አለኝ የሚል ወገን ወይም እርሱ ባልተከፈለት ሁኔታ በመካሄድ ላይ ባለ ክርክር የተሰጠ ፍርድ ጋር በተያያዘ መብት ወይም እርሱ ባልተካፈለበት ሁኔታ በመካሄድ ላይ ባለ ክርክር መብቱ (ጥቅሙ) የሚጎዳበት ሰው በክርሩ በመግባት መብቱን በህግ አግባብ ሊያስከብር ስለሚችልበት ሁኔታ
- ✓ ከላይ በተመለከተውና ባልተካፈልኩበት ክርክር የተሰጠ ፍርድ ስርዓትን ባለመከተል የተሰጠ ፍርድ ስርአቱን ባለመከተል የተሰጠ ነው በሚል ምክንያት ብቻ ፍርዱን ወደጎን በመተው በሌላ ጊዜ በሚሰጥ አዲስ ፍርድ እንዲቀየር ለማድረግ የሚ.ስችል ለ፣.
- ✓ የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አንቀጽ 41፣358፣ 212 (መዝ.ቁ. 67127 ቅጽ 13)

ሶስተኛ ወገን ተከሳሽ

- ✓ ሁለትና በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል ክርክር ሲደረግ ሶስተኛ ወገን ወደክርክሩ እንዲገባ ተከሳሽ ለፍርድ ቤቱ ሊያመለክትና ፍ/ቤቱ ሶስተኛ ወገን የተባለው ሰው ወደክርክሩ እንዲገባ ሊያዝ ይችላል።(አንቀጽ 43)
- ✓ ሶስተኛ ወገን ተከሳሽ የተባለው ሰው ሀላፊ የሚሆነው ለተከሳሽ ነው። ምክንያቱም ከሳሽ ሶስተኛ ወገን ተከሳሽ ላይ ክስ ስላላቀረበ ክስ ካላቀረበበት ሰው ላይ ውሳኔ ሊሰጥ አይችልም። ሶስተኛ ወገን ለተከሳሽ ሃለፊ የሚሆንበት ሁኔታና መጠን ካለ በዚሁ ድርሻው ልክ ለተከሳሽ ሀላፊ እንዲሆን ሊደረግ ይችላል።

የቀጠለ

- ✓ በአንቀጽ 43 መሰረት ወደክርክር እንዲገባ የተደረገ 3ኛ ወገን በክርሩ ሂደት ሊያነሳ ስለሚችላቸው የክርክር ዓይነትና አድማስ
- ✓ 3ኛ ወገን ሊያነሳ የሚችላቸው የክርክር ፊርጆች በአንድ በኩል ከተከሳሽ ጋር ሆኖ ድርሻ ክፍያ ወይም ስለተከሳሽ ሆኖ የካሳ ክፍያ የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን ተቀብሎ በተከሳሽ እግር ተተክቶ ተከሳሽ ለከሳሽ ሀላፊነት አለበት የሚባል ቢሆን እንኳን ሊካፈል የሚገባው የካሳ ክፍያ መጠን ላይ ከከሳሽ ጋር ንጽጽር በማድረግ መሟገት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ድርሻ ወይም ካሳ ለመክፈል ለከተከሳሽ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ የለብኝም በማለት መከራከር ስለመቻላቸው

የቀጠለ

- ✓ 3ኛ ወገን ጣልቃ ገብ በክርክርሂደት መሚገት የሚችለው ከተከሳሽ ጋር ብቻ ለነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ አንቀጽ 43 አስፈላጊነት ተከታታይ ክስ ሳይኖር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች በአንድ ላይ አንዲታዩ በማድረግ የሀላፊነት መጠኑን አንዲሁም ከፋዩን ወገን በመለየት የመጨረሻ እልባት ለመስጠት ስለመሆኑ
- ✓ አንቀጽ 43 መሰረት ጣልቃ የሚገባ ወገን ከመነሻውም ከተከሳሹ ጋር የህግ ወይም የውል ግንኙነት የለኝም በማለት ክርክር ያቀረበ አንደሀነ በመካሄድ ላይ ባለው ክርክር ተሳታፊ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የማይኖር ስለመሆኑና ይህን መሰል ክርክር ራሱን በቻለ ሌላ መዝገብ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ አንቀጽ 43(1) ፣ 76 (መዝ.ቁ. 79465 ቅጽ 14)

የቀጠለ

- ✓ አንድ ተከራካሪ ወገን ሌላ ተከራካሪ ግለሰብ ወደ ክርክር አንዲገባ በህጉ አግባብ መጠየቁ ተገቢ ቢሆንም ጉዳዩ መታየት ያለበት ከግለሰቡ መብት አንጻር ሳይሆን ከፍትሀብሄር ስነ-ስርዓት ህጉ ዓለማና ግብ አንጻርም ስለመሆኑ መዝ.ቁ. 96943(ቅጽ 18)

የቀጠለ

- ✓ ተከሳሽ ሶስተኛ ወገን ተከሳሽ ወደክሱ ይግባልን በሚል ሲያመለክት ሶስተኛ ወገን ተከሳሽ ሀላፊነት አለበት የሚልብትን ምክንነትና ድርሻውን በመልሱ ላይ መግለጽ ይገባዋል።
- ✓ ፍ/ቤቱ ሶስተኛ ወገን ተከሳሽ ወደክርክሩ አንዲገባ ከወሰነ ክሱንና ነተከሳሽን መልስ አብሮ መላክ ይኖርበታል።
- ✓ ሶስተኛ ወገን ተከሳሽ ተቃውሞ ካለው ከመልሱ ጋር መግለጽ ይገባዋል አንጂ መልሱን ሳያቀርብ መቅረት ጉዳት ተተስከትላል።

የቀጠለ

- ✓ ተከሳሽ ሶስተኛ ወገን ተከሳሽ ወደክርክሩ እንዲገባ ካደረገ በሆላ ከክርክሩ ይውጣልን የሚል አቤቱታ ቢያቀርብ የለም ለከሳሽ ጥቅም ሲባል ስለሆነ የገባው ሊወጣ አይገባም የሚል ክርክር ውሳኔ ሊሰጥ ይችላልን።
- ✓ ሶስተኛ ወገን ተከሳሽ ወደክርክሩ ከገባ በሆላ ክርክር የሚያደርገው ከማንጋር ነው። ተከሳሽ የማነውን ሶስተኛ ወገን ተከሳሽ ክዶ መከራከር ይችላልን።

የቀጠለ

- ✓ ሶስተኛ ወገን ተከሳሽን ክስ አግባብነት መሰረት አድርጎ ክርክር ማድርግ ይችላልወይ የለው መታየት ይኖርበታል። በተለይም ከፍ.ስ.ስህ.ቁ 76 አንጻር ክርክር ባላደረገበት ሁኔታ ሃለፊነት አለበት ድርሻውን ለኪፍል አይገባም የሚል ውሳኔ ቢሰጥ ፍትሀዊ ይሆናልን የሚል ጥያቄ ያስነሳል። የፍ.ስ.ስህ.ቁ. 43(2) የእንግሊዘኛው ቅጂ የሚያመለክተው ሶስተና ወገን ተከሳሽ ሸራሱን ድርሻ ጭምር ብቻ ሳይሆን ተከሳሽ ለከሳሽ ሀላፊ አይደለም የሚል ክርክር ጭምር ሊያነሳ እንደሚችል ያመለክታል።

የቀጠለ

- ✓ ሶስተኛ ወገን ተከሳሽ ከከሳሽ ጋር ያለውን ግላዊ ግንኙነት መሰረት አድርጎ ማቅረብ አይገባውም ከዚያ ይልቅ በቀረበው ክርክር ላይ ብቻ ማተኮር ይኖርበታል።
- ✓ አንዳንድ ባለሙያዎች እንደሚሉት ሶስተኛ ወገን ተከሳሽ ለከሳሽ ጥቅም እንደመጠራቱ ተከሳሽ ያመነውን ክዶ መከራከር የለበትም የሚሉ አሉ።

ስለመጥሪያ፣ ተቃውሞና የተቃውሞ አቀራረብ

- ✓ የመጥሪያ ስርዓት አደራረስ በፍ.ስ.ስ.ሀ.ቁ. 94-110 ለተለያዩ አካላት የመጥሪያ አደራረስ ስርዓትን ለማስቀመጥ ሞክሮል።
- ✓ አንድ ተከሳሽ ክስ/አቤቱታ የቀረበበት መሆኑን አውቆ ተገቢውን መልስና ክርክር ማድረግ ይችል ዘንድ ህጉ ባስቀመጠው ቅደም ተከተል መጥሪያ ሊደርሰው ይገባል። (የመሰማት መብት)

የቀጠለ

- ✓ መጥሪያ ደርሶት በቀጠሮው ካልቀረበ ተከሳሽ ላይ ህጉ በዘረጋው መርህ መሰረት ጉዳዩን ለመከራከር እንዳልፈለገ ተቆጥሮ ክርክሩ በሌለበት ይታያል።
- ✓ የመጥሪያ አደራረስ ቅደም ተከተሎች
- ✓ ለተከሳሽ በግል የመስጠት ዘዴ (personal service)፣ አማራጭ የመጥሪያ አሰጣጥ ዘዴ(constructive service)፣ በፖስታ ስለሚላክ መጥሪያ፣ ምትክ መጥሪያ (substituted service)

የቀጠለ

- በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 103 መሰረት ተከሳሽ በአድራሻው ስላልተገኘ ወይም ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆነ በቃለ መሀላ አስደግፎ መጥሪያውን ለፍርድ ቤ ይመልሳል። በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 105 መሰረት በምትክ አሰጣጥ ዘዴ ላይ ፍርድ ቤቱ የትኛውን መንገድ ልከተል በሚል የተሸውን መንገድ የመምረጥ የፍርድ ቤቱ ስልጣን ነው።

የቀጠለ

- ✓ መጥሪያ በአግባቡ አለመድረስ የሚያስከትለው ውጤት የተከሳሽን የመከላከል መብት ስለሚገድብ (due process of law) ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል።
- ✓ ፍርድ ቤቱ መጥሪያ በአግባቡ አለመድረን ከገመተ በ70(ለ) መሰረት በድጋሚ ሊያዝ ይችላል
- ✓ ተከሳሽ መጥሪያ በአግባቡ አለመድረሱን በማረጋገጥ በፍ.ስ.ስ.ህ.ቁ. 78 መሰረት አቤቱታ አቅርቦ በሌለበት የተሰጠውን ፍርድ ማስነሳትና ወደክርክከ ልግባ ማለት ይችላል።

የቀጠለ

- ✓ መጥሪያ በህጉ አግባብ እንዲደርሰው ሳይደረግ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ትእዛዝ የተሰጠበት ወገን ትእዛዙ እንዲነሳለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተገቢነት ላው ስለመሆኑ አንቀጽ 94-110፣70(ሀ)፣78 (መዘ.ቁ. 53113 ቅጽ 12)

የቀጠለ

- ✓ ለአንድ የመንግስት ተቋም የተላከ መጥሪያ በአግባቡ ለሚለመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች ካልደረሰ በስተቀር መጥሪያው ለተቋሙ መዝገብ ቤት ገቢ መደረጉ ብቻ መጥሪያው እንደደረሰው ተቆጥሮ ክርክሩ ተቋሙ በሌለበት ሊታይ የማይገባ ስለመሆኑ አንቀጽ 70(ሀ)፣ 70(2)፣ 96፣ 102፣ መዝ.ቁ. (100673 ቅጽ 17)

የቀጠለ

- በ78(2) መሰረት የቀረበን አቤቱታ በሚመለከት ከሳሽን መጥራት ሳያስፈልግ ፍ/ቤቱ ውድቅ ማድረግ ይችላልን የሚለው ነው። በተለይም ከመዝገቡ ጋር የተያዘዘው ማስረጃ እንደሚያመለክተው ተከሳሽ መጥሪያ ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆኑ በበርካታ መንገዶች መጥሪረረ እንዲደርሰው የተደረገ መሆኑን ቢያረጋግጥ ከሳሽ በአቤቱታው ላይ አስተያዬት እንዲሰጥ ይደረገልን

ተቃውሞና የተቃውሞ አቀራረብ

- ✓ በፍ.ስ.ስ.ህ.ቁ. 234 መሰረት ተከሳሽ መልሱን አዘጋጅቶ መቅረብ ይገባዋል።
- ✓ ተከሳሽ በመልሱ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን ጨምሮ አለኝ የሚለውን የፍሬ ነገር ክርክር ከተገቢው የማስረጃ ዝርዝር ጋር ለፍርድ ቤቱ ማቅረብ ይገባዋል።
- ✓ የመጀመሪያ መቃወሚያ የሚባሉት በዋናነት በፍ.ስ.ስ.ህ.ቁ 244 ስር ረተዘረዘሩት ናቸው

የቀጠለ

- በአንድ ጉዳይ ተከሳሽ የሆነ ወገን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ካቀረበ ፍርድ ቤቱ ከቀረቡት ክሶች መካከል በስረ-ነገር ስልጣኑ ስር ያሉትን መርጦ ለማየትና ከስረ-ነገር ስልጣኑ ባላይ የሆነውን ጉዳይ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይቅረብ በማለት የከሳሽን ክስና የተከሳሽን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተነጣጥለው እንደታዩ በማድረግ የሚሰጠው ትእዛዝ ተገቢ ስላለመሆኑ አንቀጽ 30(1)፣ 324(1-ሀ)፣ 45(2)፣ 215(2)፣ 17(3) መዝ.ቁ. 83169(ቅጽ 15)

የቀጠለ

- ✓ ተከራካሪ ወገኖች በአቤቱታቸው ላይ የጠቀሷቸውን የሰው ማስረጃዎች ሊለውጡ የሚችሉበት አግባብ አንቀጽ 223(2)፣ 234 (መዝ.ቁ. 45984 ቅጽ 9)
- ✓ አንድን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ተለይቶ የተመለከተ ማስረጃ እንዲቀርብ ህጉ ካላስገደደ በቀር ይህንን ፍሬ ነገር በማንኛውም የማስረጃ ዓይነት ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ (መዝ.ቁ. 47551 ቅጽ 9)

የቀጠለ

- ✓ማናቸውም ተከራካሪ ወገን በመከላከያ መልሱ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የተከሰሰበትን ነገር በሙለ ወይም በከፊል የሚያምን መሆኑን የገለጸ እንደሆነ ወይም በሚደረግ ምርመራ የእምነት ቃሉን የሰጠ እንደሆነ ፍ/ቤቱ በታመነው ነገር ላይ ብቻ ፍርድ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ፣ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 83 ፣234/1/ /ሠ/፣ 241 እና 242 (መዝ.ቁ 107217 ቅጽ 20)

የቀጠለ

- ✓ ተከሳሽ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል የሚያምን መሆኑን የገለፀ እንደሆነ በእምነቱ መሰረት ይገባኛል የሚለው ማናቸውም ዳኝነት እንዲሰጠው አመልካች(ከሳሽ) ሊጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ (መዝ.ቁ 109206 ቅጽ 19)

የቀጠለ

- ክስ የቀረበበት ወገን ክሱን ለማስተባበል የሚቆጥራቸው ማስረጃዎችን ተቀብሎ አለመስማት የመከላከል ህጋዊ መብትን የሚያጣብብ ስለመሆኑ አንቀጽ 223፣234፣137፣ 249፣256 (መዝ.ቁ. 49660 ቅጽ 9)

የቀጠለ

- በ244 ስር የተዘረዘሩት መቃወሚያዎች ብቻ ላይሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ የዳኝነት አልተከፈለም፣ ከሳሽ በጉዳዩ ላይ ጥቅም የለውም(33)፣ከሳሽ ችሎታ የለውም (ችሎታ ከሌለው 34 መሰረት በተወካይ ካላቀረበ) በራሱ ማቅረብ አይችልም ብዙ የክስ ምክንያቶች አላግባብ ተጣምረዋል (220) ወይም ከዚህ በፊት አብሮ ሊቀረብ ይገባ የነበረ ክስ ከሳሽ ሆነብሎ የተወውን ተነጣጥሎ የቀረበ ነው (216)እና ሌሎችን መቃወሚያዎች ሊነሱ ይችላሉ።

የቀጠለ

- ✓በ244 ስር የተጠቀሱት መቃወሚያዎች በተከራካሪ ወገን ወይም እንደ ሁኔታው በፍርድ ቤቱ ሊነሱ የሚችሉ ይሆናሉ።
- ✓በፍርድ ቤት ሊነሱ ሰሚችሉት መቃወሚያዎች የትኞቹ ናቸው።
- ✓ጥያቄዎች ገጽ 38

የቀጠለ

- ✓ አንድን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ የሚመለከት ፍርድ ቤት በቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ አግባብነት ያላቸው ምስክሮች ሳይሰሙ ወይም አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ሳይቀርቡ በመቃወሚያው ላይ ውሳኔ መስጠት የማይቻል በሚሆን ጊዜ ፍ/ቤቱ እነዚህ ማስረጃዎች እንዲቀርቡለት ትእዛዝ መስጠት የሚችል ስለመሆኑ፡- የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244(1) እና 245(1) (መዝ.ቁ 105869 ቅጽ 18)

የቀጠለ

- ✓ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ሲያስቸግር ማስረጃ መስማት አስፈላጊ ሲሆን የሚሰማበት ሀኔታ አንቀጽ 244(1)፣245(1) (መዝ.ቁ. 101689 ቅጽ 18)
- ✓ ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቶች የቀረበላቸውን ጉዳይ ለማስተናገድ ስልጣን ያላቸው ወይም የሌላቸው መሆኑን በመመርመር ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ አንቀጽ 9(2) (መዝ.ቁ. 38452 ቅጽ 12)

የቀጠለ

- ✓ ተከሳሽ በመልሱ ላይ በፍሬ ነገር ደረጃ መልስ ሲሰጥ ክሱን በግልጽ መካድ ይገባዋል (አንቀጽ 83)
- ✓ ማስረጃዎችን ሁሉ መዘርዝርና ማቅረብ እንዲሁም በእጁ የሌሉትን በፍርድ ቤቱ አንዲቀርቡለት ማድረግ ይኖርበታል። በከሳሽ በኩል የቀረቡ ማስረጃዎች ለተከሳሽ የሚጠቅሙ ከሆነም ይህንኑ ገልጾ እንዲመለከትልት ፍርድ ቤቱን ይጠቃል።

የቀጠለ

- ✓ አንድ ተከራካሪ ወገን በመከላከያ መልስ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ያመነ እንደሆነ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን በዚህ እምነት መሰረት ውሳኔ እንዲሰተው መጠየቅ እንደሚችል እና ፍ/ቤትም ሌላ በማስረጃ የሚረጋገጥ ነገር ቢኖርም እንኳን በታመናውና ውሳኔ እንዲሰጥበት በተጠየቀው ጉዳይ ብቻ ፍርድ መስጠት የሚገባው ስለመሆኑ አንቀጽ 242 (መዝ.ቁ.138717 ቅጽ 22)

የቀጠለ

- ✓ በግልጽ ያልተካደ ፍሬ ነገር እንደታመነ ይቆጠራል የሚለውን ስነ-ስርዓት ህግ ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነው ተከሳሽ ቀርቦ ክርክሩን ባሰማ ጊዜ ስለመሆኑና ድንጋጌው የካሳ ጥያቄ ጋር በተያያዘ ተፈጻሚነት የሌለው ስለመሆኑ አንቀጽ 235(2)፣ 83

(ቅጽ 9)

የቀጠለ

- ✓ ተከሳሽ በከሳሽ ላይ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የሚያቀረብ ከሆነና በፍርድ ቤቱ ስልጣን ስር የሚያርፍ ከሆነ ተገቢውን ዳኝነት በመክፈል አቤቱታውን ከመልሱ ጋር አብሮ ያቀርባል። (አንቀጽ 234(1-ረ)። እንዲሁም የተከሳሽ ክስ ለማቅረብ ዳኝነቱ የበሰለ መሆን የሚገባው ስለመሆኑ።
- ✓ የተከሳሽ ከሳሽ ክስ ሊቀርብ የሚችለው በከሳሽ ወገን ላይ ብቻ ስለመሆኑ፣ ተከሳሽ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ሲያቀርብ ሊከተለው ስለሚገባ ስነ-ስርዓት (የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 30፣36፣ 224፣ 234(1-ረ) መዝ.ቁ 102668(ቅጽ 21)

የቀጠለ

- ✓ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የፍትሀብሄር ስነ-ስርዓት ህጉ በሚያዘው መሰረት ስርዓቱን ጠብቆ ያልቀረበ ከሆነ ዳኝነት ሊሰጥበት የማይችል ስለመሆኑ አንቀጽ 234(1)(2) (መዝ.ቁ. 94713 ቅጽ 17)

የቀጠለ

- ✓ ተከራካሪ ወገኖች በቅድሚያ ሊያቀርቧቸው የሚችሉ ማስረጃዎች በክርክር ሆነ ብለው ወይም በቸልተኝነት ያላቀረቧቸውን በክርክር ሂደት ሁሉ እያንጠባጠቡ ሊያቀረቡ ወይም የማስረጃ ማሰባሰብ ስራውን ፍርድ ቤት እንዲያከናውን ሊጠይቁ የሚችሉበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ
- ✓ በፍርድ ቤት ትእዛዝ ማስረጃ የማቅረብ ተከራካሪ ወገኖች ማቅረብ የማይችሉ መሆኑ ሲረጋገጥ እና ማስረጃው ለክርክሩ ጠቃሚ መሆኑ ከታመነበት ስለመሆኑ አንቀጽ 234(1) መዝ.ቁ. 85468(ቅጽ 15)

የቀጠለ

- ✓ ተከሳሽ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ካለው የማቻቸል ጥያቄ ማቅረብ ይኖርበታል (አንቀጽ 236)
- ✓ ይህም ፍርድ ቤቱ ክርክሮችን አጣምሮ በማየት የተከራካሪዎችን ጉልበት፣ ጊዜ፣ ገንዘብ አንዲሁም የፍርድ ቤቱን ወጭና ጉልበት ይቆጥባል።

ክስ ስለመስማት

- ✓በ233 መሰረት የከሳሽ ክስ ጉድለት የሌለበት መሆኑ ከተረጋገጠ ለተከሳሽ መጥሪያ ከክሱ ጋር ከተላከለት በሆላ መልሱን ይዞ ይቀርባል።
- ✓በፍርድ ቤት ክስ የመሰረተ ወገን የክስ መስማቱ ሂደት ከመጀመሩ በፊት ክሱን በማንሳት ቀሪው ገንዘብ ሊመለስለት የሚገባ ስለመሆኑ አንቀጽ 232(1-ለ)፣ 245(4)(3)፣ 278(1)፣ የህግ ክፍል ማስታወቂያ 177/74 አንቀጽ (መዝ.ቁ. 76786 ቅጽ 13)

የቀጠለ

- የአንቀጽ 241 አላማ ተከራካሪ ወገኖች በጽሁፍ ያቀረቡት ክርክር ለማብራራት እና በፍ/ስ/ስ/ስ/ቁ. 246-248 መሰረት ጭብጥ ለመመስረት እንዲያግዝ እንጂ በጽሁፍ ማመልከቻ ላይ ያልሰፈረን የዳኝነት ጥያቄ ተከራካሪዎች እንዲያቀርቡ የሚያስችል ስላለመሆኑ አንቀጽ 222፣ 234፣ 235-236፣ 83፣ 224፣ 182፣ 241፣ 246-248፣ 251፣ 255፣ (መዝ.ቁ. 86510 (ቅጽ 15)

የቀጠለ

- በ241 መሰረት ዳኛው ክስና መልሱን በንባብ ካሰማ በሆላ ጉዳዩን መመርመር ይጀምራል። ይህ ተግባር በተለምዶ ቅድመ ክስ መስማት(first hearing) በሚል ይታወቃል። የዳኛው ቀን ሲሆን ግራ ቀኙን በመመርመር ዳኘው ለክስ መስማት የሚዘጋጅበትና ተከራካሪዎች የተለያዩበትን ጭብጥ ለማውጣት የሚጠቅም ሀደት ነው።

የቀጠለ

- ✓ የክርክር ጭብጥ የሚመሰረተው ከሳሽ የሚያቀርበውን ክስና ማስረጃ በተከሳሽ የቀረበውን የመከላከያ መልስና ማስረጃ እንዲሁም ፍርድ ቤቱ የቃል ምርመራ ሲያደረግ የሚያገኘውን ፍሬ ጉዳይ መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ አንቀጽ 241፣ 248 (መዝ.ቁ. 47252 ቅጽ 9)

የቀጠለ

- ✓ በክስ ጉዳይ ካሳ የጠየቀው ወገን ገንዘቡና በማስረጃ ባላረጋገጥበት ሁሌታ ሌላኛው ወገን ዝም በማለቱ ብቻ እንዳመነ ተቆጥሮ የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢ ስላለመሆኑ አንቀጽ 83 (መዝ.ቁ. 111599 ቅጽ 18)

የቀጠለ

- ✓ የቃል ክርክር ለመስማት እና የጽሁፍ መልስ ለመቀበል በሚል ፍ/ቤቶች በአንድ ቀጠሮ ሁለት ተግባራትን ለማከናወን የሚሰቱት ትእዛዝ ከስነ-ስርዓት ውጭ ስለመሆኑ (መዝ.ቁ. 36380 ቅጽ 8)

የቀጠለ

- ✓ ከሳሽና ተከሳሽ ያልተካካዱበትና ከሳሽ በክሱ ገልፆ ተከሳሽ ባመነው ነጥብ ላይ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ማስረጃ በመመዘን ሳይሆን ተከሳሹ በሰጠው የእምነት ቃል ወይም መልስ መሰረት መወሰን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.242 (መዝ.ቁ 112927 ቅጽ 17)
- ✓ በፍ/ሥ/ሥ/ህጉ በግልፅ ያልተካደ ፍሬ ነገር እንደታመነ ይቆጠራል የሚለው ድንጋጌ በልዩ ስርዓት(በአጭር ሁኔታ) ለሚመሩ ክርክሮች ላይ ጭምር የቀረበ መልስ ላይም ተፈፃሚ የሚሆን ስለመሆኑ፤ ፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 284 (ሀ) (መዝ.ቁ 121387 ቅጽ 20)

የቀጠለ

- ✓ክስ መስማት ሲባል ክስና መልሱን ተከራካሪዎቹ በችሎት በቃል እዲደግሙ ሳይሆን ፍ/ቤቱ የክርክሩን ጭብጥ ለይቶ ከመጣ በሆላ በአከራካሪው ጉዳይ ላይ ተከራካሪዎች ባለመብትንነኝ ወይም ሃፊ ልሆን አይገባኝም በሚለው ላይ ክርክር የሚያደርጉበት ነው።
- ✓ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ የሚክድ በግልጽ መካድ አንዳለበት ከ234-235 ባሉት ድንጋጌዎች ተመልክቶል።

የቀጠለ

- ✓ተከሳሽ የከሳሽን ክርክር አምኖ ከቀረበ በ242 እና 254 መሰረት ማስረጃ መስማት ሳያስፈልግ ውሳኔ በመጀመሪያው ቀን ቀጠሮ መስጠት ይቻላል።
- ✓ክስ ለመስማት ተከራካሪ ወገኖች መኖር አለባቸው። ተከራካሪ ወገኖች ካልቀረቡ ክስ መስማት ስለማይቻልና ዳኛው መጠየቅ ቀጣችው ሰው ስለማይኖር ጉዳዩን በሌሉበት ከማየት ጀምሮ የተለያዩ እርምጃዎችን ለመውሰድ ይችላል።

የቀጠለ

- ✓ አንቀጽበ69(2) መሰረት ክስ ለማስማት በተቀጠረበት ቀን ግራ ቀኙ ተካራከሪ ወገኖች ካልቀረቡ መዝገቡን መዝጋት የችላል። ክርክሩ በይግባኝ ላይ ከሆነ ይግባኙ ይሰረዛል። የሰበር አቤቱታ ላይ ከሆነስ
- ✓ ክሱ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ከሳሽ ሳይቀርብ ተከሳሽ ቀርቦ ክሱን ከካደ መዝገቡ ይዘጋል። ነገር ግን ተከሳሽ ክሱን ካመነ በእምነቱ መሰረት ይወሰናል።(አንቀጽ 73)

የቀጠለ

- ✓ ተከራካሪ ወገኖች ካልቀረቡ ፍ/ቤቱ ቀጠሮ መለወጥ አይገባውም። መዝገቡን መዝጋት የሚገባ ነው።
- ✓ በአንቀጽ 74 መሰረት በአንቀጽ 69(2)ና በ70(መ) መሰረት መዝገቡ ከተዘጋ ከሳሽ ምክንያት በማቅረብ ተገቢውን የዳኝነትና ወጭ በመክፈል መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ ለማድረግ ይችላል።
- ✓ የክስ መዝገብ(የይግባኝ) መዘጋትና መሰረዝ ያላቸው ውጤት በጣም የተለያዬ ነው።

የቀጠለ

- በአንቀጽ 69(2) እና በአንቀጽ 70(መ) መሰረት መዝገብ ከተዘጋ ይህንን ክስ አንደገና ለመቀጠል በሚቀርበው አቤቱታ ላይ ተፈጻሚነት ያለው ድንጋጌ አቀጽ 71 ነው።
- አንቀጽ 74 ይግባኙ የተሰረዘው በይግባኝ ባይ አለመቅረብ ወይም ለመልስ ሰጭ መጥሪያ ባለማድረስ ከሆነ መዝገቡ አንዲንቀሰቀስ አቤቱታ የሚቀርበው በአንቀጽ 74 መሰረት ነው።

ስለጭብጥ አመሰራረት

- ✓በአንቀጽ 249 መሰረት ፍ/ቤቱ ጭብጥ ለመመስረት እንዲደደስችለው የጽሁፍና ሰው ምስክሮችን ሊሰማ ይችላል።
- በአንቀጽ 251 መሰረት ፍ/ቤቱ ተካራካሪዎቹ የያዙትን ጭብጥ ለመሰረዝ፣ ለማሻሻል ይችላል

ክስ ስለመስማትና ምስክሮችን ስለመመርመር

- ✓ ሙግትን የመጀመር መብት ያለው ከሳሽ ነው (አንቀጽ 258) ነገር ግን ተከሳሽ የሚጀምርበት ሁኔታም በዚሁ ደንጋጌ ስር ተመልክቶል።
- ✓ በአንቀጽ 259 መሰረት የክስን ስለመስትና ማስረጃ ስለማቅረብ
- ✓ በአንቀጽ 261 መሰረት ምስክር ማሰማት የሚጀምረው ስራ ሙግቱን የጀመረው ነው
- ✓ በዚሁ ደንጋገ ንኡስ ቁጥር 2 መሰረት ስለራሱ ጉዳይ ምስክርነት መሰጠት የፈለሀገ መብት አለው

የቀጠለ

መዝ.ቁ. 114816

- ተከሳሽ ያቀረበውን ክስ አምኖ ነገር ግን ህግ ወይም ፍሬ ነገር በመጥቀስ የቀረበብን ክስ ዋጋ የለውም ብሎ የሚከራከር ከሆነ ሙግቱን የሚጀምረው ተከሳሽ ስለመሆኑ የፍ/ስ/ስ/ህ.ቁ. 258(1)

የቀጠለ

- ✓ በፍትሀብሄር ክርክር ማስረጃ የሚሰማውና ፍሬ ነገሩ እንዲጣራ የሚደረገው በማስረጃ የሚነጥረው ነገር ለዳኝነት አሰጣጡ እጅጉን አስፈላጊና የግድ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ፣
- ✓ ማስረጃ እንዲሰማ የሚፈልግ ወገን የማስረጃውን ዓይነትና የሚገኝበትን ቦታ ሁሉ በመጥቀስና በእጁ ላይ ያለውንም አያይዞ ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ አንቀጽ 223፣234፣137(3)፣145፣256፣ 136፣-138፣ 246፣ 248 መዝ.ቁ. 77983(ቅጽ 15)
- ✓ ፍርድ ቤቶች ለቀረበላቸው ጉዳይ አወሳሰን የጠራ ፍሬ ነገር የሌለ መሆኑን የተገነዘቡ ከሆነ ይሄው ፍሬ ነገር እንዲጣራ ተገቢ ነው ያሉትን ማጣራት ሁሉ ለማድረግ ስለመቻላቸው አንቀጽ 136፣137፣ 272፣ 327(3) ፣ 345 መዝ.ቁ. 72980(ቅጽ 15)

የቀጠለ

- ✓ በአንቀጽ 264 መሰረት ተከራካሪ ወገኖች ካቀረቦቸው ማስረጃዎች ውጭ ፍ/ቤቱ ይልቅ፣ ካለ የሌሎች ምስክሮቸን ወይም ሌሎች የጽሁፍ ማስረጃዎች አንዲቀርቡ ሊያዝ ይችላል።
- ✓ ፍርድ ቤቶች ከውሳኔ ሊደርሱ የሚገባው የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት ፣ የመከላከል ብሎም በእኩልነት መርህ የመዳኘት መብት በጠበቀ መልኩ ስለመሆኑ (መዝ.ቁ. 52546 ቅጽ 12)

በአጭር ስነ-ስርዓት የሚቀርብ ክስ

- ✓ በዚህ ስነ-ስርዓት የሚቀርቡ ጉዳዮችን በተመከለተ ከአንቀጽ 284-292 ስር ባሉት ድብጋጌዎች ተመልክተል
- ✓ በአጭር ስነ-ስርዓት የሚቀርቡ ጉዳዮች ህግ አውጭው ያስቀመጣቸው ሲሆኑ እነዚህም አንቀጽ 284 ስር ተዘርዝረዋል። እነዚህም ከሳሽ ከተከሳሽ ላይ የሚፈልገው ጥሬ ገንዘብ ከነወለዱ ወይም ያለወለድ ወይም ልኩ ተለይቶ የታወቀ ሲሆን

የቀጠለ

- ✓ አንቀጽ 284 በክስ ማመልከቻው መስፈር ስለሚገባቸው ጉዳዮች ተዘርዝረዋል።

ከሳሽ ከተከሳሽ ላይ የሚጠይቀው ሂሳብ/ገንዘብ / ከነወለዱ ወይም ከወለድ ውጭ ልኩ ተወስኖ የታወቀ

- በተለይም በውል መሰረት በግልጽ በተደረገ ውል
- በነገሩ አካባቢ ሁኔታ በሚመሰረት ውል
- በሀዋላ ወረቀት
- ገንዘብ አለኝ በሚል ሰነድ

የቀጠለ

- ቼክ ወይም ተራ የሆነ ባለእዳነትን የሚገልጽ ውል
- በግዴታ ሰነድ ወይም በተጠራ ሂሳብ ሰነድ ላይ በተመሰረተ ስምምነት ላይ
- ክሱ በቃለ መሀላ ተደግፎ መቅረብ አለበት
- የመሀላ ቃሉም ደግፎ የሚያረጋግጠው የነገሩን ትክክለኛነት፣ የተጠየቀውን ገንዘብ እውነተኛነት
- ተከሳሹም ለነገሩ ማናቸውንም ዓይነት መከላከያ እንደሌለው ከሳሽ የሚያምንበት መሆኑን

የቀጠለ

- ✓ አንቀጽ 285 ተከሳሹ መጥሪያ ደርሶት ካልቀረበ ጉዳዩ በሌለበት ይታያል ተከሳሹም ለመከላከል እንዲፈቀድለት መጠየቅ የሚችለውን እድል ያጣል
- ✓ 285(2) ተከሳሽ ቀርቦ ለመከላከል እንዲፈቀድልት ካልጠየቀ ፍ/ቤቱ ለከሳሽ ይወስናል

የቀጠለ

- አንቀጽ 286 ቀርቦ ለመከላከል ፈቃድ እንዲሰጥ ስለሚቀርብ ማመልከቻ
- ተከሳሹ የሚያቀርበው የማስፈቀጃ መከላከያ በቃለ መሀላ የተደገፈ መሆን አለበት።
- መከላከያውም የቀረበውን ክስ በሙሉ ወይም በከፊል የሚመለከት መሆኑን መግለጽ ይኖርበታል
- ነገሩን የሚከላከለው በከፊል ሲሆን ይህንኑ የሚመለከተውን መግለጽ ይኖርበታል።

የቀጠለ

- አንቀጽ 287 ተከሳሹ ለመካለክል እንዲፈቀድለት ያቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነት ሲያጣ ፍ/ቤቱ ወዲያውኑ ለከሳሽ ይፈርዳል
- አንቀጽ 290 መከላከል ስለሚፈቀድበት ሁኔታ
- የመከላከል ፈቃድ ሲሰጥ በቅድመ ሁኔታ ላይ በተመሰረተ ሊሆን ወይም ላለለሆን ይችላል። ለምሳሌ ዋስትና ወይም ገንዘቡ በፍርድ ቤት ስለሚያዝበት ሁኔታ ክሱ መቼ አንደሚሰማና መሰል ትእዛዞችን ሊሰጥ ይችላል።

የቀጠለ

- ✓ አንቀጽ 290 ፍርድን ስለማገድ
- ✓ ፍርዱ ከተሰጠ በሆላ ለተከሳሽ መጥሪያ በአግባቡ አለመድረሱን ፍርድ ቤቱ ተተረዳው እንደሆነ ፍርዱ እንዳይፈጸም ለማገድ ይችላል።

የተፋጠነ ስነ-ስርዓት

- ✓ከአንቀጽ 300-314
- ✓አንቀጽ 301 ክስ ስለሚቀርብበት ሁኔታ
- ✓ለክሱ መነሻና ለአቤቱታው መሰረት የሆነው ነገር በተፈጸመ በ 15 ቀን ውስጥ
- ✓አቤቱታውን ለማቅረብ ያለውን ስልጣን ለአቤቱታው መሰረት የሆነውን ህግና አቤቱታው የቀረበበትን ምክንያት የሚገልጽ በመሀለ ቃል የተደገፈ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት

የቀጠለ

- አንቀጽ 302 ማመልከቻው ተቀባይነት የሚያጣበት ሁኔታ
- አንቀጽ 305 በተፋጠነ ስነ-ስርዓት የሚቀርቡ ጉዳዮች
- አንቀጽ 306 በተፋጠነ ስነ-ስርዓት በታዩ ጉዳዮች ይግባኝ አይቀርብም

የተፋጠነ (summary procedure)የፍርድ ስነ-ስርዓት

- ✓ የተፋጠነ የፍርድ ስነ ስርዓት አጭር ስነ-ስርዓትና የተፋጠነ ስነ-ስርኣት በሚል የሚከፈል ነው።
- ✓ አጭር ስነ-ስርዓት ክስን በአጭር ስነ-ስርዓት ለማቅረብ በሚቻክበት ጊዜ ይህንን ስነ-ስርዓት በመጠቀም ከሳሽ ላመቅረብ መብት አለው።

የቀጠለ

- ✓ በአንቀጽ 286 መሰረት ተከሳሽ ለመከላከል ፈቃድ እንዲሰጠው አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል። (አቤቱታውን ለማቅረብ መጥሪያ በደረሰው በ 10 ቀናት ውስጥ መሆን ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ በሌለበት ይወሰናል።)
- ✓ ተከሳሽ ያቀረበው የመከላከያ ማስፈቀጃ ተቀባይነት ካገኘ መልሱን እንዲሰጥ ይፈቀድለታል
- ✓ የመከላከያ ማስፈቀጃው ተቀባይነት ከሌለው ፍ/ቤቱ ወዲያውኑ ለከሳሹ ይፈርዳል(አንቀጽ 287)

በተፋጠነ ስነ-ስርዓት (accelratede procedure) የሚታዩ ጉዳዮች

- ✓ በተፋጠነ ስነ-ስርዓት የሚቀርቡ ጉዳያደች በህግ ተለይተው የተወሰኑ አቤቱታዎች የሚታዩበት ነው።
- ✓ በተፋጠነ ስነ-ስርዓት የሚቀርቡ ጉዳዮች በአብዛኛው ተከሳሽ በጉዳዩ ላይ መልስ እንዲሰጥ ሳይጠራ ፍ/ቤቱ የራሱን ምርመራ አድርጎ ውሳኔ የሚሰጥባቸው ናቸው።
- ✓ በተፋጠነ-ስነ ስርዓት የቀረበን ጉዳይ ፍ/ቤቱ በዚህ ስነ-ስርዓት ሊቀርብ አይገባም በሚል ከወሰነ በመደበኛ ስነ-ስርኣት ክስ ሊቀርብ ይችላል።

የቀጠለ

- ✓ በተፋጠነ ስነ-ስርዓት የሚታዩ ጉዳዮች አቀረረረብና የጉዳዮቹ አይነት በአንቀጽ 301-3014 ባሉት ድንጋጌዎች የሚመሩ ናቸው።
- ✓ ጉዳዮቹም በዋናነት በአንቀጽ 305፣307፣314 ስር የተመለከቱት ናቸው።
- ✓ በተፋጠነ ስነ-ስርዓት ላይ ሌላ ተከራካሪ ወገን አለ ተብሎ ስለማይታሰብ ክርክርና መልስ አይደረግም ሆኖም በተሰጠው ትእዛዝ ወይም ውሳኔ መብቴ ተነክቶል የሚለው ሰው በ 358 መሰረት ተቃውሞውን ሊያቀርብ ይችላል።

የቀጠለ

- ✓ በተፋጠነ ስነ-ስርዓት በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ ይግባኝ አይባልም ምናልባት ለቀረበው ማመልከቻ መሰረት የሆነው ህግ ይግባኝ ማለትን የሚፈቅድ ካልሆነ በስተቀር
- ✓ በተለይም ውሳኔው የተሰጠው በፍ/ህ/ቁ. 488 መሰረት የሲቪክ ማህበራትን ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔን ወይም በንግድ ህግ 416 መሰረት የንግድ ማህበራትን ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔን ለማሻር ወይም ነአንድን ድርጅት ሸሪክ ወይም ስራ አስኪያጅ ወይም የአደራ ንብረት አስተዳዳሪን ከስራው ለማስወገድ በፍ/ህ.ቁ 522 ወይም ብንግድ ህግ ቁጥር 261 እና 293 መሰረት ሲሆን ሽርክናን ወይም የንግድ ድርጅትን ለማፍረስ በተሰጠ ውሳኔ ላይ ካልሆነ በስተቀር

የቀጠለ

- ✓ የተፋጠነ ስነ-ስርዓት የክርክር አመራር የሰዎችን የመከላከልና የመሰማት ህገ መንግስታዊ መብትን በሚነካ መልኩ መተርጎም እና ስራ ላይ ማዋል የማይገባው ስለመሆኑ አንቀጽ 284-287 (መዝ.ቁ. 131498 ቅጽ 22)

ስለእግድ

- ✓ከፍርድ በፊት ስለሚሰጥ የእስራት ትእዛዝ
- ✓አንቀጽ 147 ፍርድ ቤት ለመቅረብ ስለሚሰጥ ዋስትና(ክርክሩ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የማይመከለት ሲሆን)

ከፍርድ በፊት ንብረት አንዲከበር ስለማድረግ

አንቀጽ 151 ተፈላጊውን እቃ ወይም ንብረት ለማቅረብ ስለሚሰጥ ዋስትና

የቀጠለ

- ✓ ሁለተኛው ደግሞ ጊዜያዊ የዕግድ ትዕዛዝ ይሰጥበት የሚባለው ንብረት የክርክሩ ምክንያት (መነሻ) ባይሆንም ተከሳሹ የባለመብቶችን ጥቅም ለመጉዳት ሲል ንብረቱን ለማጥፋት፣ ለሌላ ሰው አሳልፎ ለመስጠት ያቀደ; የዛተ ወይም ያሰበ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ነው።
- ✓ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 157 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ጊዜያዊ የዕግድ ትዕዛዝ ከሳሹ በቃለመሃላ በሚያረጋግጠው አቤቱታ መነሻ በመሆኑ ተከሳሹ በቃለ መሃላ የተዘረዘሩት ፍሬ ነገሮች በእውነት ላይ የተመረኮዙ አይደለም በማለት የሚያስተባብል ከሆነ አስቅድሞ የተሰጠውን የዕግድ ትዕዛዝ ማስነሳት የሚቻልበት ሥርዓትም በቁጥር 158 ተቀምጧል።

ለጊዜው ስለሚሰጥ የማገድ ትእዛዝ

- አንቀጽ 154 የማገድ ትእዛዝ ለጊዜው ስለሚሰጥበት ሁኔታ(ከአንቀጽ 154-176)

ስለይግባኝ፣ ፍርድን ስለመቃወምና ፍርድ አንዲጣራ ወይም እንዲሻሻል ስለሚቀርብአቤቱታ

- ✓ጉዳዩን ላየው ፍርድ ቤት የሚቀርብ አቤቱታ እቅድ 6፣ 78፣207-2012፣ 358

<u>ይግባኝ</u>

አንቀጽ 320(2) በተሰጠ ፍርድ ወይም ትእዛዝ ላይ ፍርዱን የሰጠው ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማረም፣ ለማሻሻል ወይም እንደገና ለማጣራት የሚችል ሲሆን የግባኝ አይባልም(ቁ.6፣207-2012፣71፣74፣78፣358)

የቀጠለ

- ✓ የፍትሀብሄር ስነ-ስርኣት ህግ ቁጥር 320(2) ስር ከተጠቀሰው መገንዘብ የሚቻለው በሙግት ሂደት የሚታዩ ስህተቶች የሚታረሙት በይግባኝ ብቻ ሳሆን ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማረም የሚችል መሆኑ በህግ ከተደነገገ ይግባኝ ማቅርብ የሚቻለው መጀመሪያ ይሄው ሁኔታ ሲሟላ ነው።

የቀጠለ

- ✓ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. አንቀጽ 6፣ 74፣ 78፣ 07 እና ተከታዮቹ፣ 358 እና መሰል ድንጋጌዎች ፍርዱን የሰተው ፍርድ ቤት ጉዳን እንደገና ላየት ስልጣን እንዳለው ያመለክተሉ።

የቀጠለ

- አንድን ክስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ገተሰጠ ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ከሻረው በሆላ የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ ተገቢውን እንዲወስን መመለስ ሲገባው ወወን ሳሰሰደርግ ፍሬ ጉዳደደን በተመለከተ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ራሱ የሚሰጠው ውሳኔ ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን ከማረጋገጥ ጋር በተያያዘ ሊፈጠር የሚችለውን ስህተት ለማሳረም ይግባኝ ይግባኝ የማቅረብ መብቱን ከማስፋት አንጻር ታይቶ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባ ስለመሆኑ(አንቀጽ 341

የቀጠለ

- አንቀጽ 358 መቃወሚያን ስለሚያቀርቡ ወገኖች
- በክርክሩ ተካፋፊፊ መሆን የሚገባው ሰው
- በክርክሩ ውስጥ ለመግባት የሚችል
- ተካፋፊፊ ባልሆነበት ክርክር የተሰተው ፍረድ መብቱን የሚነካበትሰው መሆን ያለበት ስለመሆኑ
- ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት

የቀጠለ

- አንቀጽ 320(3) ይግባኝ የማይባልባቸው ጉዳዮች
- አንቀጽ 320(4) ውሳኔው እርን የሚመለከት ሲሆን ይግባኝ ማለት የሚቻል ስለመሆኑ
- አንቀጽ 323 ይግባኝ ስለሚቀርብበት ጊዜና አቀራረብ ስነ-ስርዓት
- አንቀጽ 324-326 ጊዜው ካለፈ በሆላ ስለሚቀርብ ይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ

የቀጠለ

- አንቀጽ 328 ይግባኝ ስለሚባልባቸው ጉዳዮች
- 328(2) ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በተለይ ካለፍቀደ በስተቀር በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አዲስ ነገር9ክርክር) ማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ
- አንቀጽ 329 ስለአዲስ ነገሮችና አዲስ ክርክሮች
- አንቀጽ 32992) እና 345 አንደተጠበቀ ሆኖ በስር ፍ/ቤት ያልተነሳ ክርክር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የማይቀርብ ስለመሆኑ

የቀጠለ

- አንቀጽ 330 የይግባኝ ማመልከቻን ስለመሰረዝ ወይም ስለማሻሻል(ፎርሙን ካልጠበቀ ሊሰረዝ ይችላል)
- አንቀጽ 331 የከሳሽ ወይም የተከሳሽ ቁጥር ከአንድ በላይ መሆንና ይግባኝ ያቀረቡት ከከሳሾች/ተከሳሾች/ የተወሰኑት ሲሆኑ ፍ/ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ ይግባን ባላቀረቡት ላይም የሚፈጸም ስለመሆኑ

ክርክርና እንዳይቀጥልና አፈጻጸም ስለማገድ

- አንቀጽ 332 ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተሚሰጠው እግድ ትእዛዝ
- አንቀጽ 334 ውሳኔ የሰጠው ፍ/ቤት ፕሬዚደንት ፍርድን የማገድ ስልጣን ያለው ስለመሆኑ
- አንቀጽ 325 ፍርድን ላገድ ስለሚቻልበት ሁኔታ ወይም ምክንያት
- አንቀጽ 337 መልስ ሰጭ ሳይጠራ ይግባኝ ስለሚሰረዝበት ሁኔታ

የቀጠለ

- አንቀጽ 340 መልስ ሰጭው በይግባኙ ላይ ስለሚያሰማው ቅሬታ
- አንቀጽ 340(1) መስቀለና ይግባኝ
- እቀጽ 341 በስር ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተዘግቶ ከሆነና ከተሸረ ከፍሬ ነገር ደረጃ አከራክሮ አንዲወሰን ስለሚመለስበት አግባብ

የቀጠለ

- ✓ አንቀጽ 343 ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤበ የነገሩን ጭብጥ አስተካክሎ ለስር ፍ/ቤት እተካክሎ መመልስ ስለመቻሉ

መዝ.ቁ. 13223 ቅጽ 2

- ✓ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ ከያዘው ጭብጥ ውጭ ጭብጡን ለውጦ ውሳኔ ስለሚሰጥበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል። አንቀጽ 182(2)፣ 342፣ 345(1-ለ)
-

የቀጠለ

- ✓ በስር ፍርድ ቤት ዳኝነት ያልተጠየቀበት ጉዳይ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ታይቶ ሊወሰን የማይችል ስለመሆኑ አንቀጽ 348(1)፣ 182) (መዝ.ቁ. 37762 ቅጽ 8)
- ✓ በስር ፍ/ቤት ያልተነሳን ክርክር መሰረት በማድረግ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ አንቀጽ 329(1)፣ 182(2) (ቅጽ 8)

የቀጠለ

- ✓ በህግ የተቀመተው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኋላ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ እንዲፈቀድ የሚቀርብ አቤቱታ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ አንቀጽ 326(2)(1)፣ 323(2) ፣ 325 መዝ.ቁ. 57360

(ቅጽ 12)

የቀጠለ

- ✓ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በተለይ ካልፈቀደ በስተቀር ይግባኝ ባይ በይግባኝ ማመልከቻ ላይ ዘርዝሮ ያልገለጸውን አዲስ ነገር በማንሳት ወይም መሰረት በማድረግ ለመከራከር የማችይል ስለመሆኑ፤
- ✓ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በይግባኝ ባይ ማመልከቻ ተዘርዝሮ ከተገለጸ ወይም ክርክር ከተነሳበት ውጭ በሆነ ነገር ፍርድ መስጠት የማይቻል ስለመሆኑ አንቀጽ 328(2-3)(መዝ.ቁ 137831 ቅጽ 22)

ወጭና ኪሳራ

ቅጽ 4

- ✓ ወጭ ኪሳራ አወሳሰን
- ✓ ስለወጭና ኪሳራ የሚመለከተው የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 462 በክስ ምክንያት ስለሚከፈሉ ማናቸውም ወጭዎችና ኪሳራዎች የሚከፍለውን ወገን፣ የወጭውንና የኪሳራውን ልክ፣ የሚከፈልበትን ሀብት ምንጭ፣ የአከፋፈሉን ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ትክክል መስሎ በሚገምተው ሁኔታ መብት (discretion) ይሰጠዋል። የወጭና ኪሳራ ክፍያ አላማም ረቺውወገን በክርክሩ ምክንያት ያወጣውን ወጭ ተረቺ እንዲሸፍን እንጂ ተረቺውን ለመቅታት ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ የወጭና ኪሳራውን መጠን ለመወሰን መብት (discretion) ቢኖረውም ውሳኔውን በሚወስንበት ጊዜ ይህንኑ የህጉን ዓላማ ከግምት ማስገባት ይኖርበታል።

የቀጠለ

- ✓ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ግምት ነው ያለውን ወጭና ኪሳራን ለመወሰን ይረዳው ዘንድም ወጭው ወይም ኪሳራው ሊከፈለው የሚገባው ወገን የወጭ ዝርዝሩን እንዲያቀርብ ሊያዘው እንደሚችል የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 463(1) ይመለከታል። ዝርዝሩ ቢቀርብለትም ግን የቀረበውን ዝርዝር እንዳለ ለመቀበል ሳገደድ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 464 መሰረት መርምሮ በቂ ባልሆነ ምክንያት ከፍ ብሎ ሚታየውን በመቀነስ ወይም ተገቢ ያልሆነውን በመቀነስ ወይም ጭርሱንም በመሰረዝ መጠኑን መወሰን እደሚገባው ይሄው የስነ-ስርዓት ድንጋጌ ያመለክታል።

የቀጠለ

- ስለዚህ ወጭና ኪሳራ ሲወሰን መብት (discretion) ቢኖረውም መተኑን ሲወሰን ምክንያታዊ ባልሆነና በተጋነነመመንገድ እንዳሆን ጥንቃቀ ሊያደርግ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ።

የቀጠለ

- ✓ የይግባኝ መዝገብ በድሀ ደንብ እንዲከፈትለት የሚቀርብ ጥያቄን ለመወሰን አመልካች ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት (ንብረት በመታገደ ፣ገንዘብ ማንቀሳቀስ የማይችል እና የሚከፍለው ገንዘብ የሌለው እንደሆነ) የዳኝነት የሚከፍለው ገንዘብ ያለው ወይም የሌለው መሆኑ መጣራት እና መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ፤የፌ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 567 ፣ፍ/ህ/ቁ 1793/ለ/ እና ህገመንግስት 37(1) (መዝ.ቁ 117754 ቅጽ 22)

የቀጠለ

- ✓ የመስቀለኛ ይግባኝ ክርክር ስለሚመራበት የህግ አግባብ በተከራካሪ ወገኖች መካከል የሚቀርብን መስቀለኛ ይግባኝን በተመለከተ በህግ በግልጽ የተቀመጠ ድንጋጌ ባለመኖሩ ምክንያት በመደበኛነት የተቀመጡት የስነ-ስርዓት ህጎች ተፈጻሚ መሆን ያለባቸው ስለመሆኑ፣ መልስ ሰችው ወገን የሚያቀርበው ይግባኝ ማመልከቻ ግልባች ለይግባኝ ባይ እንዲደርስ የሚደረገው ይግባኙ ያልተሰረዘ ከሆ ብቻ ስለመሆኑ አንቀጽ 213(1)፣ 337፣ 338፣ 340(2) (መዝ.ቁ. 92043 ቅጽ 16)

ወጭና ኪሳራ

- ✓ በወጭና ኪሳራ ጉዳይ በተሰጠ ውሳኔ ላይ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ አንቀጽ 466 (መዝ.ቁ. 98593 ቅጽ 17)
- ✓ የወጭና ኪሳራ ክርክር ጉዳይ ሊወሰን የሚገባበት በዋናው መዝገብ ስለመሆኑ አንቀጽ 183፣ 378፣ 462-464 (መዝ.ቁ. 83701 ቅጽ 14)

የቀጠለ

- ✓ ከወጭና ኪሳራ አወሳሰን ጋር በተገናኘ ከቅን ልቦና ውጭ ለክርክር የተዳረገ ወገን የክርክሩ ረቺ መሆኑ እስከታወቀ ድረስ ቅን ልቦና ስለሌለው ወገን በክርክሩ ምክንያት የወጣውን ወጭ እንዲተካለት በሚል ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ
- ✓ የወጭና ኪሳራ ጥያቄን አስመልክቶ ፍርድ ቤቶች በመጠኑ ላይ ለመወሰን በህግ ስልጣን የተሰጣቸው ስለመሆኑና ረቺ የሆነ ወገን ሁልጊዜ ወጭና ኪሳራ ሊወሰን ይገባል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ አንቀጽ 462-464 (መዝ.ቁ. 91103 ቅጽ 15)

አንዳንድ ነጥቦች ስለፍርድ አፈጻጸም

- የፍርድ አፈፃፀም መሠረታዊ ታሳቢዎችና ያጋጠሙ ችግሮች
- አፈፃፀም ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ በራሱ አማካኝነት ወደ ተግባር የሚለውጥበት ሥርዓት ነው። ስለፍርድ አፈፃፀም የተደነገጉትን ድንጋጌዎች በመከተል ፍርድን በተግባር መተርጎም እንደመሆኑ መጠን የማስፈፀሚያ ሥርዓቱ በጥቅሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ ሕጉን መሠረታዊ ዓላማ ተከትሎ #በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲፈፀም በሚያስችል አኳኋን የተዋቀረ ነው።

የቀጠለ

- ይሁን እንጂ በተግባር እንደሚታየው ክስ አቅርቦ ለማስፈረድ ከሚወሰደው ወጭ; ጊዜና ጉልበት ባልተናነሰ ሁኔታ የተፈረደን ፍርድ ለማስፈፀም የሚጠይቀው ወጭና ጊዜ በልጦ የሚታይበት ጊዜ ይከሰታል። ምክንያቶቹ በርካታ ናቸው።
- ከነዚህም ጥቂቶቹ፡-
- - በተፈረደው ፍርድ ላይ የይግባኝ አቤቱታ በመቅረቡ ምክንያት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 332-335 መሠረት በሚሰጠው የማገጃ ትዕዛዝ፤
- - ፍርድ በማስፈፀም ሂደት ከርህራሄነት የተነሣ ሕጉ የሚያዘውን በጥብቅ ከመከተል ይልቅ በራስ ህሊና የመመራት አዝማሚያ መታየቱ፤

የቀጠለ

- - በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 445-447 መሠረት በሽያጭ አፈፃፀም ጊዜ የሥነ ሥርዓት ጉደለት አለ በሚል ሳቢያ የሚነሳው ክርክር
- - በተከበረ ወይም በተያዘ ንብረት ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ባለይዞታ ነኝ ባይ የሚያቀርበው አቤቱታ፤
- - ገዥው የገዛበትን ገንዘብ በሕግ በተወሰነው ጊዜ አለመክፈል ... ወዘተ የመሳሰሉት ይገኙበታል።

የቀጠለ

- በአጠቃላይ ፍርድን በማስፈፀም በኩል ለሚከሰተው መጓተት ዓበይት የሆኑትን ምክንያቶች በሦስት ከፍሎ ማየት ይቻላል።
- ይኸውም፥-
- ሕጉ በሚያዘው መሠረት ያለመመራት፣ በሕጉ እና በልምድ መካከል ያለው ልዩነት፣
- ድንጋጌው በራሱ ግልፅ ያለመሆን ወይም ሁሉን ሁኔታ ያለመሸፈን

የቀጠለ

ባለመብት ፍርድ እንዲፈፀምለት በቁጥር 378 መሠረት ማመልከቻ ሲያቀርብ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት በቁጥር 386 መሠረት እንደፍርዱ የማይፈፅምበት ምክንያት ካለው ያስረዳ ዘንድ የማመልከቻው ግልባጭ ከመጥሪያ ጋር ይላክለታል።

- በቀነ ቀጠሮውም በቀረበ ጊዜ ፍርድ ቤቱና የፍርድ ባለገንዘቡ ለሚያቀርቡለት ጥያቄ በመሃላ ቃል የተደገፈ መልስ ይሰጣል በማለት በቁጥር 386(1) እና (2) ተደንግጓል። በዚህ አኳኋን መፈፀም ሲገባው የፍርድ ባለዕዳው ለቀረበበት የአፈፃፀም ክስ መልሱን ይዞ እንዲቀርብ፤ ይዞ በቀረበ ጊዜም የፍርድ ባለመብቱ የመልስ መልሱን እንዲያቀርብ ተከታታይ ቀጠሮ የመስጠቱ አሠራር በህግ ያልተደገፈ እና አላስፈላጊ ተግባር ነው።

የቀጠለ

- በአፈፃፀም ምክንያት የሚነሳው ክርክር አጭርና ግልፅ ነው ። ይኸዉም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 375፣396፣397፣398 መሠረት ዕዳውን ከፍሎ ከሆነ፣ የፍርድ ባለዕዳነቱን ግዴታ ፈፅሞ ከሆነ፣ የመቻቻል ጥያቄ ካለው ይህንኑ ለማረጋገጥ እና ፍርዱ የሚፈፀምበትን መንገድ የሚያሳይ ከሆነ ብቻ ነው። ስለሆነም ሌላ የፅሑፍ ክርክርን የሚጋብዝበት ሁኔታ አይታይም። ይህም ከላይ ከፍ ሲል እንደተገለፀው የፍርድ ባለዕዳው በአካል በተገኘበት ጊዜ በመሃላ ሥር ሆኖ የሚያረጋግጠው ተግባር ነው።

የቀጠለ

- በዚህ አኳኋን ፍርዱ እንዳይፈፀም የሚቃወምበትን ምክንያት ቀርቦ ካላስረዳ ወይንም ያልቀረበ እንደሆነ በቁጥር 386(3) እና 392(1) መሠረት ፍ/ቤቱ ውሳኔው እንዲፈፀም ወዲያውኑ ትዕዛዝ መስጠት አለበት።

የቀጠለ

- መውጣት፣ ለመሸሸና ለመሰወር ያቀደ መሆኑን የሚያረጋግጥ በቃለ መሃላ የተደገፈ ማመልከቻ የቀረበለት እንደሆነ በቁጥር 386(1) መሠረት መጥሪያ ማስተላለፍ ሳያስፈልግ በቀጥታ ታስሮ እንዲቀርብ እና እንደፍርዱ የማይፈፀምበትን ምክንያት እንዲያስረዳ ፍ/ቤቱ ማዘዝ እንደሚችልም በቁጥር 387 ተመልክቷል። ስለሆነም በመጀመሪያው ቀን ቀጠሮ በዚህ አኳኋን እንደ ህጉ አነጋገር የአፈፃፀም ሥርዓቱ ከተከናወነ አፈፃፀምን ሳይንዛዛ መምራት እና በአጭር ጊዜ ለመቋጨት ያስችላል።

የቀጠለ

- በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ከተዘረዘሩት ድንጋጌዎች መካከል ግልፅ ያልሆነ ወይም ሁሉን ሁኔታዎች የማይሸፍኑ ወይም በትርጉም ስራ ምክንያት በተፈጠረው ክፍተት ለጉዳዩ መጓተት ምክንያት የሆኑትን ድንጋጌዎች ለአብነት ለመጥቀስ ያህል፡-የፍርድ ባለዕዳው በመጥሪያው መሠረት ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ታስሮ እንዲቀርብና ለሚደረግለት ጥያቄ ወይም ምርመራ መልስ እንዲሰጥ የሚታዘዘው ገንዘብ እንዲከፍል የተፈረደን ፍርድ ለማስፈፀም እንደሆነ ከዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 3 እና 4 መገንዘብ ይቻላል።

የቀጠለ

- እንደዚሁም የፍርድ ባለዕዳው ፍርዱ እንዳይፈፀም መሰናክል በመፍጠር ወይም የፍርዱን አፈፃፀም ለማዘግየት ንብረቱን ከፍርድ ቤቱ ሥልጣን ክልል ውጭ ለማሸሽ ወይም ራሱ ከፍርድ ቤቱ ሥልጣን ክልል ውጭ ለ
- ፍርዱን እንዲያስፈፅም የታዘዘ ፍ/ቤት ስላለው ሥልጣን በሚደነግገገው በቁጥር 347(1)“...ስለፍርድ አፈፃፀም የሚሰጠው ትዕዛዝና በትዕዛዙም ላይ ይግባኝ ስለሚባልበት ሁኔታ ያለው ሥልጣን ዋናውን ፍርድ ከወሰነው ፍርድ ፍ/ቤት ሥልጣን ጋር ዕኩል ሆኖ ይቆጠራል።” በማለት በመደንገጉ አፈፃፀሙን በሚመለከት የይግባኝ አቤቱታ ለየትኛው ፍ/ቤት ይቀርባል? ለሚለው ጥያቄ አሳሳች ምላሽ የሚሰጥ ድንጋጌ ሆኖ እናገኘዋለን።

የቀጠለ

- ፍርዱን የሰጠው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ቢሆንና ፍርዱን እንዲያስፈፅም የተወከለው ደግሞ የወረዳው ፍ/ቤት ቢሆን ከወረዳው ፍ/ቤት ይግባኝ ስለሚባልበት ሁኔታ ያለው ሥልጣን ከከፍተኛው ፍ/ቤት ሥልጣን ጋር ዕኩል ሆኖ ይቆጠራል በማለት በቁጥር 374(1) የተቀመጠ ስለሆነ በአፈፃፀሙ ጉዳይ የወረዳው ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ላይ ይግባኙ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይቀርባል ወደ ሚለው መደምደሚያ የሚያደርስ ነው።

የቀጠለ

- ይሁን እንጂ ከዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዘኛ ግልባጭ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ዕኩል ሆኖ የሚቆጠረው በማስፈፀም ረገድ ያለውን ሥልጣን በሚመለከት እንጂ #ይግባኝ በተባለ ጊዜ ራሱ የተወከለው ፍ/ቤት በሚሰጠው ፍርድ ይግባኝ ሲባል ይግባኙን ለሚያየው ፍ/ቤት ነው በማለት ደንግጓል።

የቀጠለ

- የፍርድ አፈፃፀምን በተወከለው ፍ/ቤት ለጊዜው አግዶ ስለማቆየት በሚደነግገው ቁጥር 376 (1) ‹‹... እንዲሁም ፍርድ እንዲታገድለት ወይም ስለፍርዱ ወይም ስለውሳኔው አፈፃፀም ጉዳይ ለፈረደው ፍ/ቤት ሲያመለክት ፍርድ ቤቱ ፍርዱን እንደሚያስፈፅመው ፍ/ቤት ሆኖ ነገሩን ይመለከታል።›› የሚለውን ከዚሁ ድንጋጌ የመጀመሪያ ክፍል ጋር አቆራኝተን ስንመለከተው ትርጉም የሚሰጥ አይደለም። ሆኖም ከእንግሊዝኛው ግልባጭ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ለአስፈፃሚው ፍ/ቤት በቂ ምክንያት የቀረበ እንደሆነ ፍርዱን የፈረደው ፍ/ቤት አፈፃፀሙን እንዲያግድለት ወይም ደግሞ እራሱ ፍርዱን የፈረደው ፍ/ቤት አፈፃፀሙን ይዞት ቢሆን ኖሮ ስለአፈፃፀሙ መስጠት ይችል የነበረውን ማናቸውም ትዕዛዝ መስጠት እንዲችል የፍርድ ባለዕዳው ውሳኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት ማመልከት እንዲችል በቂ ሆኖ ለሚገመት ጊዜ ብቻ ውሳኔው ከመፈፀሙ ታግዶ እንዲቆይ ያደርግለታል የሚለውን ለማስተላለፍ ታስቦ እንደሆነ እንረዳለን፣

የቀጠለ

- ይህም ፍርዱን የፈረደው ፍ/ቤት ሥልጣኑን ሙሉ በሙሉ አለማስተላለፉንና አስፈፃሚው ፍ/ቤትም ለዘለቄታው ማገድ የማይችል መሆኑን የሚያሳይ ነው።
- ድንጋጌው በራሱ ግልፅ ባለመሆኑ የተነሣ አሻሚ ትርጉም ሊሰጥ በመቻሉ ለክርክር መራዘም ምክንያት ከሆኑ ድንጋጌዎች አንዱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 የተመለከተው ነው። ቁጥር 377 "ፍርድ በተፈረደለት በማናቸወም ሰው ላይ ፍርድ የተፈረደበት ወገን ክስ ያቀረበበት እንደሆነ ፍ/ቤቱ ተገቢ መስሎ የገመተውን በቂ ዋስትና ወይም መያዣ እንዲሰጥ ካደረገ በኃላ ለክርክሩ ውሳኔ እስኪሰጠው ድረስ ፍርዱ ከመፈፀሙ ታግዶ እንዲቆይ ለማዘዝ ይችላል።" በሚል በመቀረፁ አፈፃፀሙ ታይቶ እንዲቆይ ትዕዛዝ የሚሰጠው የትኛው ፍ/ቤት ነው? የፍርድ ባለዕዳው በፍርድ ባለገንዘቡ ላይ ያቀረበውን ክስ እያየ ያለው ፍ/ቤት ወይስ አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት? ለሚለው ጥያቄ ድንጋጌው ለብቻው ሲታይ አሻሚ ነው።

የቀጠለ

- ፍርድ እንዲፈፀም የሚቀርብ ማመልከቻ በጊዜ የተገደበ ለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 384 ተመልክቷል። በቁጥር 385(1) "ፍርድ እንዲፈፀም የሚቀርበው ማመልከቻ ከዚህ በላይ ባሉት ቁጥሮች የተነገሩትን ግዴታዎችና ሥርዓቶች አሟልቶ የያዘ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ማረጋገጥ አለበት።" በማለት በመደንገጉና የይርጋ ጊዜው ሁኔታ ከቁጥር 385 በፊት የተቀመጠ በመሆኑ ጊዜው ያለፈበት የአፈፃፀም ጥያቄ ከሆነ እንደሌሎች የይርጋ ክርክሮች በተከራካሪ ወገን ብቻ እንዲቀርብ የተተወ ሳይሆን #ፍ/ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ሊያነሳው የሚገባ ጉደይ ነው። የጊዜውም መነሻ የሚታሰበው እንዲፈፀም የሚጠይቀው ነገር በፍርዱ #ከተወሰነበት ቀንና ዓመተ ምህረት ጀምሮ ነው በሚል ተቀምጧል። ፍርድ ሲባል በመጀሪያ ደረጃ የተሰጠን ፍርድ ወይም በይግባኝ የተሰጠን ፍርድ ያጠቃላል የሚለውንም ጥያቄ የሚያስነሳ ነው።
- ከፍርድ በፊት እና በፍርድ ማስፈጸም ሒደት ስለሚሰጡ የዕግድ ትዕዛዞች

የቀጠለ

- ✓ በሕግ አተረጓጎም መርህ መሠረት ሕጉ አሻሚ መስሎ በታየ ጊዜ ድንጋጌዎችን እርስ በእርሳቸው አስተሳስረን ልንተረጉም ይገባል። ይኸው ድንጋጌ የሚገኝበት ክፍል አፈፃፀምን ስለሚያስፈፅሙ ፍ/ቤቶች እና ስላላቸው ሥልጣን የሚገልፅ በመሆኑ በዚሁ ድንጋጌ "... ፍርድ ቤቱ... " የሚለው ሀረግ አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት መሆኑን እንረዳለን ከዚህም በቀር ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት የዕግድ ትዕዛዝ የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 154-159 በተመለከቱት ሁኔታዎች በመሆኑና የተጀመረን አፈፃፀምም አግዶ የሚያቆየው በዚሁ ህግ በቁጥር 332-335 በተመለከተው መሠረት የይግባኝ ክርክሩን የሚያየው ፍ/ቤት በመሆኑ በማናቸውም መንገድ ቢሆን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 377 ድንጋጌ የፍርድ ባለዕዳው በፍርድ ባለመብቱ ላይ ክስ በማቅረቡ ምክንያት ክሱን እያየ ያለው ፍ/ቤት በሌላ ፍ/ቤት በፍርድ ባለዕዳው ላይ የተጀመረን የአፈፃፀም ክስ አግዶ ለማቆየት ሥልጣን የሚሰጥ አይደለም።

የቀጠለ

- ፍርድ እንዲፈፀም የሚቀርብ ማመልከቻ በጊዜ የተገደበ ለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 384 ተመልክቷል። በቁጥር 385(1) "ፍርድ እንዲፈፀም የሚቀርበው ማመልከቻ ከዚህ በላይ ባሉት ቁጥሮች የተነገሩትን ግዴታዎችና ሥርዓቶች አሟልቶ የያዘ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ማረጋገጥ አለበት።" በማለት በመደንገጉና የይርጋ ጊዜው ሁኔታ ከቁጥር 385 በፊት የተቀመጠ በመሆኑ ጊዜው ያለፈበት የአፈፃፀም ጥያቄ ከሆነ እንደሌሎች የይርጋ ክርክሮች በተከራካሪ ወገን ብቻ እንዲቀርብ የተተወ ሳይሆን #ፍ/ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ሊያነሳው የሚገባ ጉደይ ነው። የጊዜውም መነሻ የሚታሰበው እንዲፈፀም የሚጠይቀው ነገር በፍርዱ #ከተወሰነበት ቀንና ዓመተ ምህረት ጀምሮ ነው በሚል ተቀምጧል። ፍርድ ሲባል በመጀሪያ ደረጃ የተሰጠን ፍርድ ወይም በይግባኝ የተሰጠን ፍርድ ያጠቃላል የሚለውንም ጥያቄ የሚያስነሳ ነው።
- ከፍርድ በፊት እና በፍርድ ማስፈጸም ሒደት ስለሚሰጡ የዕግድ ትዕዛዞች

የቀጠለ

1. ለጊዜው የሚሰጥ የማገድ ትዕዛዝ (temporary junction) ክርክሩ ተጀምሮ ነገሩ በፍርድ እስኪወሰን ወይም የተለየ ትዕዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ያሉትን ሁኔታዎች በነበሩበት አኳኃን ጠብቆ ለማቆየት ሲባል ከሚሰጡት ጊዜያዊ ትዕዛዞች አንዱ ነው። ንብረት እንዳለ እንዲቆይ፣ ከመጥፋት እንዲድን፣ እንዳይበላሽ፣ ለሌላ ሰው ተላልፎ እንዳይሰጥ ወደ ሌላ ስፍራ እንዳይዛወር እንዳይባክን ለማድረግ ሲሆን ዓላማውም ክርክሩ ተጠናቆ የሚሰጥ ፍርድ ለአፈፃፀሙ ዋስትና እንዲኖረው፤ ውጤት እንዲያገኝ ለማስቻል ነው።

የቀጠለ

- ይህ ዓይነቱ ትዕዛዝ የሚሰጠውም ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ በሚያየው ፍ/ቤት ሲሆን ትዕዛዙ በሁለት ምክንያቶች ላይ የተመሠረተ ነው።
- አንደኛው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 154(ለ) እንደተጠቀሰው ጊዜያዊ የማገጃ ትዕዛዝ የሚሰጠው በክርክሩ ምክንያት በሆነው ንብረት ላይ ሆኖ ይኸው ክርክር የተነሣበት ንብረት የሚጠፋ፣ የሚበላሽ ወይም ተከሳሹ በማናቸውም ምክንያት ለሌላ አሳልፎ ለመስጠት ያቀደ መሆኑ በቃለ መሃላ ሲረጋገጥ ሲሆን፤

የቀጠለ

የቀጠለ

- አፋጻጸም ከአንቀጽ 371-461
- ✓ አንድ ለእዳ መክፈያነት በአፈጻጸም በጨረታ እንዲሸጥ በተደረገ ንብረት ጨረታ ላይ በመከላከል የጨረታው አሸናፊ ከሆነ በኋላ የጨረታ ሽያጩን ለመፈጸም ያልቻለ ወገን ንብረቱ በቀጣይ በጨረታ ሊሸጥ የተገኘው የሽያጭ ዋጋ ዝቅተኛ የሆነ እንደሆነ የመጀመሪያው ጨረታ አሸናፊ ለተከሰተው የዋጋ ልዩነት የዋጋ ልዩነት ለፍርድ ባለእዳው በካሳ መልክ ለመካፈል የሚገደድ ስለመሆኑ አንቀጽ 429 (መዝ.ቁ. 72017 ቅጽ 14)

የቀጠለ

መዝ.ቁ. 15672 ቅጽ2

- በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 442 መሰረት ንብረት ለምን ያክል ጊዜ በድጋሚ እንደሚሸጥ በፍርድ ቤቱ እንደሚታዘዝ ባይደነግግም ንብረቱ ገዢ አያገኝም ወደሚል መደምደሚያ ኤደርስም። ሁለት ጊዜ ጨረታ ወጥቶ አሸናፊዎቹ ገንዘቡን ከፍለው ካልወሰዱ ለ3ኛ ጊዜ ጨረታ ሊወጣ ይገባል የሚል ውሳኔ ተሰጥቷል። አንድ ጨረታ ያሸነፈ ሰው በ 15 ቀን ውስጥ ገንዘቡን ከፍሎ ንብረቱን መውሰድ ያለበት ሲሆን ገንዘቡን ገቢ ካላደረገ 2ኛ ጨረታ ይወጣል። ገቢ ባያደርግ ለምን ያክል ጊዜ ጨረታ ሲወጣ ይኖራል የሚለው ጥያቄ የሚነሳ ነው። ለምን ያክል ጊዜ ፣ ንብረቱን ይረከብ ብሎ መወሰንስ ምን ያክል ተገቢ ነው።

የቀጠለ

መዝ.ቁ. 18199 ቅጽ 2

- በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 429 መሰረት በሀራጭ ጨረታውን ያሸነፈው ገዥ ዋጋውን እንዲከፍል ማስገደድ አይቻልም። ገዥው በጨረታ ላሸነፈው ንብረት ገንዘቡን ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ ጨረታው እንደተሰረዘ ተቆጥሮ ሌላ ጨረታ ይወጣል። በፍርድ አፈጻጸም ንብረትን የመሸጥ ስነ-ስርዓት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ከቁጥር 422-431 ስር የተመለከቱት ናቸው። አንቀጽ 429 ንብረቱን ያሸነፈው ገዥ ገንዘቡን ለመክፈል ፈቃደና እንዲከፍል አይገደድም በማለት ስቀምጣል። ነገር ግን ሁለተኛ ጨረታ ወጥቶ ከመጀመሪያው ጨረታ ያነሰ ከሆነ ልዩነቱንና ኪሳራ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል።